3) ሀብት ለክርስቲያን መሪዎች አደገኛ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው?

ረ. 1) የክርስቲያን ሕይወት ጦርነት የሚመስለው እንዴት ነው?

2) ጠላቶቻችን እነማናቸው?

3) የጦር ዕቃዎቻችን ምንድናቸው?

4) ድልን የምንቀዳጀው እንዴት ነው?

5. ጸሎት

ትምህርት ሰባት

ዘፍጥረት 16-19

የመጀመሪያ ቀን ዘፍጥረት 16

እስካሁን የእግዚአብሔር ወዳጅና የእምነት ሰው የሆነውን የአብራምን ሕይወት እያጠናን ነበር። ባለፈው ሳምንት፥ እግዚአብሔር ለአብራም ልጅና የከነዓን ምድር እንደሚሰጠው የተስፋ ቃል በመግባት፥ እንዴት ዘላለማዊ ቃል ኪዳን እንዳደረገ ተመልክተናል። መጽሐፍ ቅዱስ «አብራም እግዚአብሔርን አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት» ይላል። የአብራም ሕይወት ባመዛኙ የእኛ ዓይነት ነው። ታላላቅ የእምነት እርምጃዎች የሚደረጉባቸው ጊዜያት አሉ፤ እንዲሁም እምነታችን ጠውልጎ በእራሳችን ፍላጎት የምንመላለስባቸው ጊዜያት አሉ። ዛሬም አብራምና ሦራ በእምነት ለመጓዝ ባለመቻላቸው፥ በውጤቱ ሕይወታቸው በሙሉ፥ የልጆቻቸው ሕይወት፥ እና ዓለሙ በሙሉ የተጎዳበትን ሌላ ምሳሌ እናያለን።

1ኛ ጥያቄ፤ ሀ) በሕይወትህ ያልተለመደ ነገር እንድታደርግ እግዚአብሔር የረዳህን ጊዜ ተናገር።

ለ) በሕይወትህ እምነትህ የደከመበትን ጊዜ ተናገር።

2ኛ ጥያቄ፤ ዘፍ. 16-19 አንብብ። ሀ) በአብራም ሕይወት ውስጥ የእምነትን መታጣት የሚጠቁሙ ክስተቶችን ዘርዝር።

ለ) በአብራም ሕይወት ውስጥ የእምነትን መኖር የሚጠቁሙ ክስተቶችን ዘርዝር።

3ኛ ጥያቄ፤ ዘፍ. 16ን አንብብ። ሀ) አብራም ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ከነዓን ምድር ከመጣ ምን ያህል ጊዜ ሆኖታል?

ለ) ሦራ ልጅ ለማግኘት የወጠነችው እቅድ ምን ነበር?

ሐ) እቅዷን ከዳር በማድረሱ በኩል አብራም የተጫወተው ሚና ምን ነበር?

መ) አብራም ምን ማድረግ ነበረበት?

ሠ) አጋር ካረገዘች በኋላ በሦራና በአጋር መካከል የነበረው ግንኙነት ምን ሆነ?

ረ) አብራም ሦራ በአጋር ላይ ምን እንድታደርግ ፈቀደላት?

ሰ) አጋርን የጎበኘው መልአክ ማን ነበር? (16፡9ን ከ 16፡13 ጋር አወዳድር)።

ሸ) የአጋር ልጅ ምን ተብሎ መጠራት ነበረበት?

ቀ) የአጋር ልጅ ምን ዓይነት መሆን ነበረበት?

በ) አጋር ለእግዚአብሔር የሰጠችው ስም ምን የሚል ነበር?

ታሪካዊ መጻሕፍት በምናጠናበት ጊዜ፥ ታሪኩን ለመረዳት መፈለግ ብቻ ሳይሆን፥ ጸሐፊው ሊያስተምረን የሚፈልገውን አቢይ ትምህርት ለማግኘት እንደምንሻ ልብ ልትል ይገባል።

4ኛ ጥያቄ፤ ከዘፍጥረት 16 የምንማረው አቢይ ትምህርት ምንድነው?

1. በአጋር በኩል ልጅ ለማግኘት አብራምና ሦራ የወጠኑት እቅድ (16፡1-4)።

እግዚአብሔር አብራምን ከጠራውና ከእርሱም ጋር ቃል ኪዳን ካደረገ እነሆ አሥር ረዥም ዓመታት አልፈዋል። እግዚአብሔር ለአብራም ሁለት ከፍተኛ ነገሮችን እንደሚያሟላለት ተስፋ ገብቶለት ነበር። በመጀመሪያ፥ የቤተሰብ የዘር ሐረጉ እንዲቀጥል የሚያደርግ

ልጅ፥ ሁለተኛ፥ የከነዓንን ምድር እንደሚሰጠው ቃል ገብቶለት ነበር። አብራም ስለ ከነዓን ምድር የተሰጠው የተስፋ ቃል ዘግየት ብሎ እስኪፈጸም ለመጠበቅ ፈቅደኛ ነበር። ዳሩ ግን አብራምና ሦራ እግዚአብሔር ልጅ እንደሚሰጣቸው የገባውን የተስፋ ቃል በመጠበቁ ረገድ ችግሮች ነበሩባቸው።

ከወንዶች ይልቅ፥ ሴቶች በስተእርጅና ልጅ ለመውለድ ያለመቻላቸው ሐቅ፥ ለእነርሱ አስጨናቂ ሸክም ነው። ሦራ በዚህ ጊዜ 75 ዓመት ያህል ሆኗት ነበር። እያንዳንዱ ዓመት ባለፈ ቁጥር ልጅ ለመውለድ የሚያስችላት ተፈጥሮአዊ ብቃቷ እየቀነሰ ይሄድ ነበር። ምንም ያህል ቁሳዊ ብልጽግና ቢኖራትም፥ ልጅ ያለመውለድ ጭንቀቷን ሊያቃልልላት አይችልም ነበር። እግዚአብሔር ለምን መካን እንዳደረጋት ባናውቅም፥ ዳሩ ግን ማህጸንዋን የዘጋው እግዚአብሔር እንደሆነ ራስዋ ትናገራለች። ምንም እንኳ እግዚአብሔር በፍርድ መልክ የሴቶችን ማህጸን ቢዘጋም (ዘፍ. 20)፥ ብዙውን ጊዜ ይህን አያደርግም። እግዚአብሔር ሦራን እንዲቀጣ ምክንያት ሊሆን የሚችል ኃጢአት በሕይወቷ አልሠራችም፤ እንዳውም ብዙ ጻድቅ ሴቶች መካን እንደነበሩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናገኛለን። ስለዚህ መካንነት ሁል ጊዜ የሚከሰተው በኃጢአት ወይም በእምነት ማጣት እንደሆነ ከመናገር መጠንቀቅ አለብን። ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔር ዓላማዎች ከእኛ የተሰወሩ ናቸው። ልጅ ለመውለድ የማይችሉትን ሴቶች ከማሳዘን ይልቅ፥ ፍቅርና ርኅራኄ ልናሳያቸው ይገባል። ምናልባት እግዚአብሔር ሁል ጊዜም ባይሆን በጸሎት ማህጸንን ይከፍት ይሆናል። ነገሮች ለእኛ በሚያመች ሁኔታ ሲከናወኑ ብቻ ሳይሆን፥ በነገር ሁሉ ለፈቃዱ ልንገዛ እንደሚገባን ልብ ማለት ያሻናል።

5ኛ ጥያቄ፤ ሀ) በቤተ ክርስቲያንህ ልጅ ለመውለድ የማይችሉትን አንዳንድ ሴቶች ስም ዘርዝር።

ለ) ይህ የሆነው በኃጢአት ወይም በእምነት ማጣት ምክንያት እንደሆነ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ይናገራሉን?

ሐ) ይህን የሚናገሩት ለምንድነው?

መ) ቤተ ክርስቲያንህ በዚህ ዓይነት የሚያዝኑትን ሰዎች እንዴት ለመረዳት ትችላለች?

እንደሰው አነጋገር፥ ሥራ ዝም ብላ ብትጠብቅ ኖሮ፥ መካን ሆና መቅረቷ ነበር። ልጅ ለማግኘት በፊቷ የነበረው ብቸኛ አማራጭ፥ በጥንት ዘመን ሰዎች ይዘወተር የነበረውን ልማድ መከተል ነበር። በጥንት ዘመን፥ አንዲት ሴት ልጅ ለመውለድ ካቃታት፥ ከሴት ባሪያዎች አንዷን ወስዳ ለባልዋ ትሰጣለች። ልጅ ከተመለደም፥ ልጁ የእመቤትዋ ልጅ እንደሆነ ተቆጥሮ ይወርሳታል።

ሥራ እግዚአብሔርን ሳትጠይቅ፥ ይህን ልጅ የማግኛ ዘዴ መረጠች፤ እግዚአብሔር ልጅ እንደሚሰጣት የገባውንም ቃል ምክንያት አድርጋ አቀረበች። ልጅ ሳትወልድ አሥር ዓመታት እንደ ዋዛ ነጉደዋል። ምናልባት እግዚአብሔር ይህንን ብልሃት እንዲጠቀሙ እየጠበቃቸው ይሆን? ሥራ ግብፃዊት የነበረችው ባሪያዋን አጋርን በመውሰድ ልጅ እንዲወልድ አብራምን ጠየቀችው። እግዚአብሔር በተአምራት እስኪገለጽ እንደመጠበቅ፥ ልጅ ለማግኘት የተለመደውን መንገድ መረጠች። በእምነት ሳይሆን በማየት ተመላለሰች። ይሁንና ተስፋ የተገባውን ልጅ ለማግኘት እነሥራ የተጓዙበትን መንገድ እግዚአብሔር ለመቀበል አልፈለገም።

የቤተሰቡ ራስ የሆነው አብራም፥ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳልነበረ መገንዘብ ነበረበት። ዳሩ ግን የባለቤቱን አሳብ መቃወም ሲገባው በእቅዱ ተስማምቶ ከአጋር ጋር ተኛ። እርስዋም ጸነሰች።

በዚህ ሁሉ፥ አብራምና ሥራ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን እንዳልጠየቁ ልብ በል። ይልቁንም በእምነት ሳይሆን በማየት ተመላለሱ። እቅዶቻቸውም ሰመሩላቸው። አብራም ልጅ ለማግኘት ቻለ። ዳሩ ግን አብራምም ሆነ ሥራ ይህ ውሳኔ የሚያስከትልባቸውን ችግር አስቀድመው ለመመልከት አልቻሉም ነበር። በእዚህ አድራጎታቸው፥ አብራምና ሥራ በሥጋው እንጂ፥ ለእግዚአብሔር በመታዘዝና በእምነት የማይመላለስ ክርስቲያን ምሳሌዎች ናቸው።

6ኛ ጥያቄ፤ ዛሬ ክርስቲያኖች በእምነት ሳይሆን፥ በማየት ሊመላለሱ የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች ግለጽ።

እዚህ ላይ የሚያስገርመው ነገር፥ ለዚህ ችግር ምንጩ፥ ከብዙ ዓመታት በፊት አብራምና ሦራ ወደ ግብፅ በወረዱ ጊዜ መጀመሩ ነው። እዚያም እንደዚሁ በእምነት ሳይሆን፥ በማየት ተመላልሰው ነበር። አጋር አብራም በግብፅ በነበረ ጊዜ ካገኛቸው ባሪያዎች አንዷ ነበረች። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ አጋር ለአብራምና ሦራ የማሰናከያ ዓለት በመሆን፥ እንዴት ለውድቀት እንደዳረገቻቸው እናያለን።

2. የሦራና አጋር አለመግባባት (14፡4-6)

በእራሳችን ብርታትና ጥበብ እንደምናደርጋቸው በርካታ ምርጫዎች፥ የአብራምና ሦራ ምርጫዎችም ወዲያውኑ ችግር መፍጠር ጀመሩ። አጋር አሁን ስላረገዘችና ልጅም ስለምትወልድለት፥ ከአብራም ሕጋዊ ሚስቶች አንዷ እንደምትሆን ማሰቧ የማይቀር ነው። ማርገዝዋም አጋርን እንድትታበይ አደረጋት። በሆነ መንገድ በሦራ መካንነት ላይ መሳለቅ ጀመረች (ለተመሳሳይ ሁኔታ 1ኛ ሳሙ. 1፡6 ተመልከት)። ከዚህም የተነሣ ሦራ ቀናችባት፤ ጠላቻትም።

7ኛ ጥያቄ፤ - አንድ ሰው ከአንድ ሚስት በላይ በሚያገባበት ቤተሰብ ውስጥ፥ የዚህ ዓይነቱ ትግል ባመዛኙ የሚከሰተው እንዴት ነው?

አብራምና ሦራ ልጅ ለማግኘት የራሳቸውን እቅድ በመወጠናቸው፥ እንዴት በሥጋ መጓዝ እንደ ቀጠሉ አስተውል። እንደ አዳምና ሔዋን ኃጢአት ሁሉ፥ የኃጢአታቸው የመጀመሪያ ፍሬ በቤተሰባቸው ውስጥ የሰላም መደፍረስ ነበር። ምንም እንኳ በመጀመሪያ የራስዋ እቅድ ቢሆንም፥ ሦራ ወደ አብራም ዞር በማለት በርስዋና በአጋር መካከል ስለተፈጠረው ችግር ወቀሰችው። አብራም ለሦራና ለአጋር ፍትሐዊ ፍርድ እንደመስጠት ሦራ በአጋር ላይ የፈለገችውን እንድታደርግ ፈቀደላት።

አጋር የአብራም ቁባት በመሆን በጥሩ ሁኔታ መኖር እንደ ጀመረች አይጠረጠርም። አሁን ግን እንደገና ወደ ባርነቷ ተመለሰች። በፊት ታዝንላት የነበረችው ሦራ አሁን ታስጨንቃት ጀመር። በኋላ እስራኤላውያን በግብፅ በባርነት ሥር የሚኖሩበትን ሁኔታ ለመግለጽ «ተጨነቁ» የሚለውን ተመሳሳይ የዕብራይስጥ ቃል ሙሴ መጠቀሙ

አስገራሚ ነው (ዘፍ. 15፡13)። አብራም ለፍትሕ ማሰብ ነበረበት። የአብራም ሚስት የመሆኑ ጉዳይ የአጋር ምርጫ አልነበረም። ዳሩ ግን ቤቱን በፍትሕ እንደማስተዳደር፥ አብራም አጋርን አላግባብ እንድትሰቃይ ፈረደባት።

8ኛ ጥያቄ፤- ችግሩን ለማቃለል፥ አብራም ምን ማድረግ የነበረበት ይመስልሃል?

አንድ ጊዜ በሥጋ መንገድ ለመጓዝ ከጀመርን፥ በመንፈስ ለእግዚአብሔር ለመታዘዝ መመለሱ ከባድ ነው። እቅዶቻችን ከግብ ሊደርሱ ቢችሉም፥ የእቅዶቻችን ውጤቶች በዙሪያችን ያሉትን ነገሮች ግጥሩት ይጀምራሉ። ቤተሰባችን፥ ሥራችን፥ የጸሎት ሕይወታን፥ ወዘተ. ሁሉ ይጎዳል። አንዱ ለሌሎች ኃጢአቶች መንገድ ይጠርጋል። ወደ እምነት ጉዞ መመለሱ ከባድ ነው። ይህ የአብራምና የሦራ ምርጫ፥ አብራም ከእግዚአሔር ጋር ለ13 ዓመታት ህብረት እንዳያደርግ ማዕቀብ ጥሎበታል። እግዚአብሔር ከአብራም ጋር ዳግመኛ ሲነጋገር የምንመለከተው ይህ ከሆነ ከ13 ዓመታት በኋላ ነው (16፡16ን እግዚአብሔር ዳግመኛ ከተናገረበት ከ17፡1 ጋር አወዳድር)።

9ኛ ጥያቄ፤- ይህ በአንተ ወይም አንተ በምታውቀው ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ የታየው እንዴት ነው?

3. የአጋር በበረሃ ውስጥ ከጌታ መልአክ ጋር መገናኘት (16፡7-14)

አጋር በሦራ ስለተገፋች፥ ወደ ምድረ በዳ ለመሸሽ ወሰነች። መልአኩ ወዴት እንደምትሄድ በጠየቃት ጊዜ ስላልመለሰችለት፥ የምትሄድበትን ሥፍራ የምታውቅ አትመስልም። የእግዚአብሔር መልአክ ያገኛት ወደ ግብፅ በሚያስሄድ መንገድ ላይ በውኃ ምንጭ አጠገብ ነበር። በአብራምና በሦራ ብትናቅም፥ እግዚአብሔር በምድረ በዳ ተገናኛት እንጂ፥ አልተዋትም።

10ኛ ጥያቄ፤- እግዚአብሔር እራሱን ለአጋር ለምን የገለጠ ይመስልሃል?

የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን የዚህን መልአክ ማንነት ብዙ አመራምሯቸዋል። በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባይስተዋልም፥

ክፍሉ የሚለው የእግዚአብሔር «መልአክ» በማለት ለይቶ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔር «መልአኩ» ነው። እዚህ ላይ የተገለጸው የታወቀ መልአክ ነው። ይኸው መልአክ፥ በብሉይ ኪዳን ውስጥ በርካታ ጊዜ ተጠቅሷል። በአዲስ ኪዳን ግን አልተጠቀሰም (ዘፍ. 18፡1-21፤ 31፡11፥ 13፤ ዘጸ. 3፡2፥4፤ መሳ. 2፡1-5፤ 6፡11-12፥ 14፤ 13፡3-23፤ ዘካ. 3፡1-6፤ 12፡8)።

እነዚህን ጥቅሶች በጥንቃቄ ብንመረምር፥ የሚከተሉትን ነገሮች እናገኛለን፡-

1. የእግዚአብሔር መልአክ የተባለው የእግዚአብሔር ልዩ መልእክተኛ ነው።

2. የእግዚአብሔር መልአክ ከእግዚአብሔር የተለየ ነው። ይህም ሲባል ስለ እግዚአብሔር እና ለእግዚአብሔር ይናገራል ማለት ነው። ይህ መልአኩ «እግዚአብሔር መቸገርሽን ሰምቶአልና» ብሎ በሚናገርበት በቁጥር 11 ላይ ታይቷል።

3. የእግዚአብሔር መልአክ፥ እንደ እግዚአብሔርም ተገልጾአል። በቁጥር 10 «ዘርሽን እጅግ አበዛለሁ» በማለት እግዚአብሔር ብቻ የሚናገረውን የተስፋ ቃል ሰጥቷል። ቁጥር 13 «እርስዋም ይናገራት የነበረውን የእግዚአብሔርን ስም ኤልሮኢ ብላ ጠራች፤ የሚያየኝን በውኑ እዚህ ደግሞ አየሁትን?» እንዳለች ይነገራል።

ይህ መልአክ ማን ሊሆን እንደሚችል ሁለት አበይት አማራጮች አሉ። በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን ሥልጣን የያዘና በፈንታውም የሚናገር ልዩ መልአክ ሊሆን ይችላል። ሁለተኛ፥ በሰው አምሳል ወደ ምድር ከመምጣቱና በቤቴልሔም ከተማ ከመወለዱ በፊት፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው መገለጹ ሊሆን ይችላል። አብዛኛዎቹ ክርስቲያኖች በዘመናት ሁሉ የዚህን መልአክ ማንነት የተረዱት በዚህ መንገድ ነው። በብሉይ ኪዳን ኢየሱስ እራሱን ለሰው ለመግለጽ፥ የእግዚአብሔር ልዩው መልአክ በመሆን ጊዜያዊ አካል እንደሚለብስና እራሱንም ገልጾ ሲያበቃ ይሰወር እንደ ነበረ ይናገራሉ። እርሱ የእግዚአብሔር መልአክም (ለመልእክተኛ)፥ እግዚአብሔርም ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ

ከተወለደ በኋላ፥ ስለዚህ ልዩ መለአክ የተገለጸ ነገር አለመኖሩ አስገራሚ ነው።

የእግዚአብሔር መልአክ፥ አጋርን በምድረ በዳ አገኛት። መልአኩ የአጋርን ስምና ከሦራ ጋር የነበራትን ግንኙነት አስቀድሞ ቢያውቅም፥ እራስዋ ስላለችበት ሁኔታ እንድትናገር ይጠይቃት ጀመር።

መልአኩ ለአጋር እያንዳንዳቸው ትንቢታዊ መልእክትን ያስከተሉ ሁለት ትዕዛዛት ሰጠ። በመጀመሪያ፥ አጋር ወደ ሦራ መመለስና ለእርስዋ መገዛት ነበረባት። መልአኩ የኑሮዋ ሁኔታ እንደሚሻሻል አልተናገረም። ዳሩ ግን ለጊዜው የእግዚአብሔር እቅድ ከአብራምና ሦራ ጋር እንድትኖር ነበር። አስቸጋሪ ትዕዛዝ ቢሆንም፥ አጋር እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ፈቃደኛ ነበረች። እግዚአብሔር እስማኤልን ታላቅ ሕዝብ እንደሚያደርገው ተስፋ ሰጠ። በእርግጥ እግዚአብሔር የአጋር ዘርዋም ለመቁጠር እስከማይቻል ድረስ እንደሚበዙ፥ ለአብራም የሰጠውን ዓይነት የተስፋ ቃል ሰጣት። የአብራም ልጅ እንደ መሆኑ እርሱም የተባረከ ነበር። ይሁንና ዘሮችዋ፥ የተስፋ ቃል ከተሰጠው ልጅ እንደሚወለዱት ሰላምን በማግኘት ፈንታ፥ በአድመኝነት የተሞሉ የሚሆኑ ነበር።

ሁለተኛ፥ መልአኩ ልጁን እስማኤል ብላ እንድትጠራው አዞአታል። እስማኤል ማለት «እግዚአብሔር ይሰማል» ማለት ነው። እግዚአብሔር ለአጋር በመከራ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ጩኸት የሚሰማ አምላክ እንደሆነ አስተምሮአታል። እግዚአብሔር በመከራ ውስጥ ያሉትን ሰዎች የማይሰማ የሩቅ አምላክ ሳይሆን፥ ሁል ጊዜም ለሰዎች ፍላጎት ትኩረት የሚሰጥ አምላክ ነው።

እንዲሁም መልአኩ የእስማኤልና የእስማኤላውያን ባሕርይ ምን እንደሚመስል ትንቢት ተናግሮአል። ሙሴ በኦሪት ዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ፥ የልጆች ባሕርይ እንዴት ከወላጆች ጋር እንደሚመሳሰል በተከታታይ ያሳያል። እስማኤልና ትውልዱ በሁለት መንገዶች ተገልጸዋል። በመጀመሪያ፥ የሚዳ አህያን መምሰል ነበረባቸው። እግዚአብሔር ይህን ሲል፥ ዘላኖች፥ በምድረ በዳ የሚቅበዘበዙና ከሌሎች ሰዎች ተለይተው እንደሚኖሩ መናገሩ ነበር። ሁለተኛ፥

ከሌሎች ጋር ጠላቶች ሆነው የሚኖሩ ሰዎች መሆን ነበረባቸው። በሦራና አጋር መካከል ጠላትነት እንደ ነበረ ሁሉ፥ እስማኤላውያንም እንዲሁ በግያቂርጥ ጠብ አጫሪነትና የውጊያ ጥማት መታወቅ ነበረባቸው። በተለይም ይህ ጠላትነት፥ የእስማኤል ወንድም ከሆነው ከይስሐቅና ከእስራኤላውያን ጋር ነበር።

11ኛ ጥያቄ፤ - የእስማኤል ትውልዶች እነማናቸው? በዛሬው ዓለም የዚህ ትንቢት ፍጻሜ የታየው እንዴት ነው?

የእስማኤል ትውልዶች የዛሬዎቹ ዐረቦች ናቸው። የመልአኩ ትንቢት በብዙ መንገዶች ተፈጽሟል። ይህም ዛሬ በዓላማችን አይሁዶችና ዐረቦች በሚያደርጉት የማያቋርጥ ትግል ውስጥ ይስተዋላል። መልአኩ እነዚህን የተሰሩ ቃሎች ከሰጣት በኋላ፥ አጋር ይህ ልዩ መልአክ እንደ ነበረ አስተዋለች። ይህ መልአክ እግዚአብሔር እንደ ነበረ ተረዳች። ኤልሮኢም ብላ ጠራችው። ትርጉሙም እግዚአብሔር ያያል ማለት ነው። ብዙውን ጊዜ ስሙን (ባሕርዩን) ለሕዝቡ የገለጸው እግዚአብሔር ሲሆን፥ እዚህ ላይ ግን አጋር ለእግዚአብሔር ስም አወጣችለት። እግዚአብሔር ለዕርዳታ የምታሰማውን የሲቃ ጩኸት መስማት ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን በሰዎች ሕይወት ውስጥ የሚፈጸሙትን ነገሮች ሁሉ የሚመለከት አምላክ እንደሆነ ተገነዘበች። እርሱ ሁል ጊዜም በችግር ውስጥ ያሉትን ሰዎች የሚመለከትና የሚረዳ አምላክ ነው።

12ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) እግዚአብሔር የሚሰማና የሚያይ አምላክ መሆኑን መረዳት ለእኛ ማበረታቻ የሚሆነን እንዴት ነው?

ለ) እግዚአብሔር በሕይወታቸው ውስጥ ለሚፈጸሙት ክስተቶች ግድ የሌለውና ከእነርሱም የራቀ እንደሆነ አድርገው የሚያምኑ ሰዎች አሉን?

ሐ) ለእንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች፥ ይህ ስም እንዴት ያጽናናቸዋል?

አጋር በውኃው ምንጭ አጠገብ ስለ ነበረች፥ የምንጩንም ስም ለውጣዋለች። ብኤርለሃይሮኢ ብላ ጠራችው። ለዚህ ስም የሚሰጡ

ሁለት የተለያዩ ትርጉሞች አሉ። «የሚያየኝ የሕያው አምላክ ጉድጓድ» ወይም «የሚያየኝን አየሁት» የሚል ሊሆን ይችላል።

13ኛ ጥያቄ፤- የእግዚአብሔር ኤልሮኢ፥ ማለትም የሚያይ አምላክ የመሆኑ እውነታ ሕይወታችንን እንዴት ሊለውጠው ይገባል?

4. የአብራም ልጅ የእስማኤል መወለድ (16፡15-16)

አጋር እግዚአብሔርን በመታዘዝ፥ አብራምና ሦራን በባርነት ወደ ግገልገሉ ተመለሰች። ሕይወቷ በአበሳ የታጀበ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም። ይሁንና ታላቅ ሕዝብ የሚሆን ልጅ እንደምትወልድ የተገባላት የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ነበራት። ምንም እንኳ ወደ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ መመለስ ቢሆንም፥ እግዚአብሔርን ስለ ታዘዘች፥ በብዙ መንገዶች አብራምና ሦራ ካደረጉት በላይ ትልቅ እምነትና መታዘዝ አሳይታለች። እስማኤል በተወለደ ጊዜ፥ ስም ያወጣው አብራም እንጂ አጋር ባለ መሆንዋ፥ ከመልአኩ ጋር እንደተገናኘች ለአብራም ነግራዋለች ማለት ነው። ይህን በማድረጉ፥ አብራም ልጁ የእራሱ አንደሆነ ለሰው ሁሉ አሳይቷል። ስለ ሦራ የተጠቀሰ ነገር ስለሌለ፥ ሦራ ልጁን እንደ ልጇ አድርጋ ለመቀበል አልፈለገችም ነበር ማለት ነው። እስማኤል በተወለደ ጊዜ፥ አብራም የ86 ዓመት ሰው ነበር። እስማኤል የተወለደው በ2080 ዓ.ዓ. ገደማ ነበር።

ይህንን ስም ለአጋርና አብራም ልጅ በመስጠት፥ እግዚአብሔር ለአብራምና ሦራ አስፈላጊ የሆነ ትምህርት ለማስተማር ፈልጎ ነበር። እስማኤልን በጠሩ ወይም ሲጠራ በሰሙ ጊዜ ሁሉ፥ እግዚአብሔር እንደሚሰማቸው በመረዳት፥ ፈቃዱን መጠየቅ የነበረባቸውን ጊዜ ያስታውሳሉ። በሥጋ የመነዳታቸውን ኃጢአት የሚያስታውሳቸው ነበር። ደግሞም በችግር ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ ሁሉ፥ ነገሮችን በእራሳቸው ጉልበት ለማከናወን ከመሞከር ይልቅ፥ ወደ እግዚአብሔር መጮህ እንዳለባቸው የሚያሳይ ቋሚ ማስታወሻ ነበር። በእግዚአብሔር ፈቃድ መመላለስ ማለት፥ ብዙ ዓመታት የሚያስጠብቅ ቢሆንም እንኳ፥ እቅዳችንን ሁሉ ለእርሱና ለእቅዶቹ በማስገዛት ነው። እግዚአብሔር

በሕይወታችን ውስጥ በሚፈጸሙት ክስተቶች ሁሉ የሚሠራ አምላክ ነው። የምናስበው ወይም የምናደርገው ነገር ሁሉ ከእግዚአብሔር ዓይን ወይም ጆሮ የተሰወረ አይደለም። ከእርሱ ልንሰውር የምንችለው ምንም ነገር የለም። ከእኛ የራቀ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ለእያንዳንዳችን የቀረበና ከእኛም ጋር ህብረት ሊያደርግ የሚሻ አምላክ ነው። እኛስ፥ በመነፈስ ወይንስ በሥጋችን ነው የምንመላለስ? ከእግዚአብሔርስ ጋር በየዕለቱ እንገናኛለንን? በሥጋ እየተመላለስን የምናደርጋቸው ውሳኔዎች ብዙውን ጊዜ የኛንና የሌሎችን ሕይወት ለረዥም ጊዜያት ያሰቃያሉ።

14ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) በሥጋ ኃይል ያደረግሃቸውን ውሳኔዎች የሚያሳዩ ምሳሌዎችን ዘርዝር።

ለ) በእግዚአብሔር ፈቃድ ያደረግሃቸውን ምርጫዎች የሚያሳዩ ምሳሌዎች ዘርዝር።

ሐ) በሥጋ ያደረግሃቸው ውሳኔዎች ንስሐ ከገባህባቸው በኋላ ለረዥም ጊዜያት ችግር ያስከተሉብህ እንዴት ነው?

አብራምና ሦራ በሥጋ እየተመላለሱ ሳሉ ያደረጉት ውሳኔ በታሪክ ሁሉ በርካታ ነገሮችን ለውጧል።

1) ስምም የነበረውን ቤተሰብ ወደ መራርነትና ግጭት ለውጧል።

2) ዛሬ በአይሁዶችና በዐረቦች መካከል የሚታየውን የጎሳ ጦርነት አስከትሏል።

3) በመጨረሻም ዛሬ በዓለም በጣም አደገኛ የሆነውን የእስልምና ሃይማኖት አስከትሏል። የሃይማኖቱም መሥራች የእስማኤል ልጅ ዘር የሆነው መሐመድ ነበር።

ክርስቲያኖች እንደመሆናችን፥ እቅዳችንንና አሳባችንን ሁሉ በሚሰማው፥ በሚያየውና በሚመልሰው አምላካችን ላይ ለማስቀመጥ መጠንቀቅ አለብን። በራሳችን ብልጠት ላለመመራት መጠንቀቅ አለብን። የዓለምን የእንቆቅልሽ መፍቻ መንገድ እንዳንከተል መጠንቀቅ አለብን። እንዲህም ካደረግን፥ ሕይወታችን ሁሉ በችግሮች የተወሳሰበ ይሆናል።

ሁለተኛ ቀን ፡- ዘፍጥረት 17

የምናመልከው እግዚአብሔር ጸጋን የተሞላና ይቅር ባይ አምላክ ነው። ምንም እንኳ አብራምና ሦራ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ የሚያደርጓቸውን ምርጫዎች ቢወስኑትም፥ ያ ማለት እግዚአብሔር ትቶአቸዋል ማለት አልነበረም። እግዚአብሔር አሁንም ለአብራም የሰጣቸውን ዘላለማዊ የተስፋ ቃሎች አልረሳቸውም። ምንም እንኳን ሰው ባይታመንም፥ እግዚአብሔር ግን ሁል ጊዜም ለተስፋ ቃሎቹ የታመነ ነው። በዘፍጥረት 17፥ እግዚአብሔር ዳግም አብራምን ፈለገና ለእርሱ የገባቸውን የቃል ኪዳን ተስፋዎች አደሰ።

15ኛ ጥያቄ፤ - ዘፍጥረት 17ን አንብብ። ሀ) እስማኤል ከተወለደ ስንት ዓመታት አልፈው ነበር?

ለ) እግዚአብሔር ለአብራም እራሱን በገለጸ ጊዜ፥ ለእራሱ የሰጠው ስም ምን ነበር?

ሐ) እግዚአብሔር ለአብራም በተገለጸ ጊዜ ምን ትዕዛዝ ሰጠው? (ቁ. 1)።

መ) እግዚአብሔር ለአብራም የሰጠው አዲስ ስም ምን ነበር? ትርጓሜውስ ምን ማለት ነበር?

ሠ) እግዚአብሔር ከአብራም ጋር ያደሳቸው ሁለት አበይት የተስፋ ቃሎች የትኞቹ ናቸው?

ረ) እግዚአብሔር ከአብራም ጋር ላደረገው የዘላለም ቃል ኪዳን ምልክት መሆን የሚገባው ምን ነበር?

ሰ) የሦራ አዲሱ ስምና የተገባላት የተስፋ ቃሎች ምንድናቸው?

ሸ) የሦራ ልጅ ማን ተብሎ መጠራት ነበረበት? ለምን?

ቀ) አብራም የሳቀው ለምን ነበር?

በ) እስማኤልን በተመለከተ፥ እግዚአብሔር የገባቸው የተስፋ ቃሎች ምንድናቸው?

ተ) አብራም ለእግዚአብሔር የነበረውን ታዛዥነት ያሳየው እንዴት ነበር?

ቸ) የዚህ ታሪክ አቢይ ትምህርት ምንድነው?

1. በእግዚአብሔርና በአብራም መካከል የነበረው ቃል ኪዳን መታደስ (17፡1-8)።

እስማኤል ከተወለደበት ጊዜ አንስቶ 13 ረጎዥም ዓመታት አልፈዋል። አብራም በቤቱ አካባቢ የሚጫወት ልጅ በማግኘቱ ሊደሰት ቢችልም፥ የእስማኤል መኖር በቤተሰቡ ውስጥ ትልቅ ውጊያ እንዳስከተለ አያጠራጥርም። በመንፈሳዊ ሁኔታ እነዚህ ለአብራም መካን የነበሩ ረጎዥም ዓመታት ነበሩ። ለአሥራ ሦስት ዓመታት አብራም እግዚአብሔርን እንዳመለከ፥ ወይም እግዚአብሔር ከአብራም ጋር እንደተገናኘ የሚጠቅስ ነገር የለም። ዳሩ ግን እግዚአብሔር አብራምን አልዘነጋውም ነበር። ከእርሱ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ለማደስና በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል የቃል ኪዳን ምልክት ለመስጠት፥ አንድ ቀን እግዚአብሔር ከአብራም ጋር ተገናኘ። ይህም የግዝረት ቃል ኪዳን ነበር።

እግዚአብሔር ከአብራም ጋር በተገናኘ ጊዜ፥ ለቃል ኪዳኑ መሠረት የሚጥል አዲስ ስም ሰጠው። ለአይሁዶች፥ ስም የእግዚአብሔርን ባሕርይ የሚገልጽ እንደሆነ ልብ በል። አዲሱ የእግዚአብሔር ስም ኤልሻዳይ የሚል ነበር። ምሁራን፥ የዚህ ስም ትርጉም በትክክል ምን ማለት እንደሆነ አያውቁም። ብዙውን ጊዜ ሁሉን ቻይ አምላክ ተብሎ ተተርጎሞአል። አንዳንድ ሰዎች የዚህ ቃል ትርጉም «ተራራው እግዚአብሔር» የሚል እንደሆነ ያስባሉ። ይህም የእግዚአብሔርን ታላቅ ኃይል፥ ወይም የእግዚአብሔርን መኖሪያ ያመለክታል [መዝ. (121)፡1]። ይህ እግዚአብሔር ባሕርዩን ለአባቶች ለመግለጽ የተጠቀመበት የተለየ ስም ነበር (ዘጸ. 6፡3 ተመልከት)። ይህ ስም ለሰው አእምሮ የማይቻል በሚመስልበት ወቅት እንኳን፥ እግዚአብሔር ተአምራት ለመሥራት ያለውን ታላቅ ኃይል የሚያመለክት ነው። ይህ በሥራ በኩል ልጅ የማግኘቱን ጉዳይ እንደማይቻል አድርጎ ለተመለከተው አብራም፥ ትልቅ ነገር ነበር።

16ኛ ጥያቄ፤ ሀ) እግዚአብሔር ማንኛውንም ነገር ለማድረግ የሚችል ሃያል የመሆኑ እውነታ፥ ለክርስቲያኖች አበረታች የሚሆነው በምን መንገድ ነው?

ለ) ክርስቲያኖች እግዚአብሔር በችግሮቻቸው፥ በመንግሥት፥ ወዘተ. ላይ ኃይል እንደሌለው አድርገው የሚቆጥሩበትን መንገዶች ዘርዝር።

እግዚአብሔር በዘፍጥረት 12 ላይ ለአብራም ቃል ኪዳን በሰጠ ጊዜ፥ ውርና ካራንን እንዲለቅ በማዘዝ ጀመረ። በዘፍጥረት 17ም፥ እግዚአብሔር ከልጆቹ ሕይወት ደስ የሚሰኝበትን አድራጎት የሚያንጸባርቅ ትዕዛዝ በድጋሚ በመስጠት ጀምሮአል- «በፊቴ ተመላለስ፤ ፍጹምም ሁን»። በዚህ ትዕዛዝ መሠረት ለአብራም የተሰጡ ሁለት መመሪያዎች ነበሩ፡- በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ፊት መመላለስ ነበረበት።

17ኛ ጥያቄ፤ ሀ) ይህ ምን ማለት ይመስልሃል?

ለ) አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር እየተመላለሰ መሆኑን እንዴት ለማሳየት ይችላል?

ሐ) ይህ በአንተስ ሕይወት ውስጥ እንዴት ይታያል?

መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ጋር ስለሚጓዝ ሰው ሲናገር፥ ያ ሰው ባለማቋረጥ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የሚስማማ ሕይወት እየኖረ ነው ማለቱ ነው። ይህም እግዚአብሔርን በማወቅ፥ እርሱን ለማስደሰት በፈቱ በግልጽና በታማኝነት መመላለስ፥ ለክብሩም ለመኖር መሻት ማለት ነው። በእግዚአብሔር ፊት የሚመላለስ ሰው፥ እራሱን ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ምሪትና ጥበቃ ሥር ያስቀምጣል። በእግዚአብሔር ምሪት ይጓዛል እንጂ፥ የራሱን እቅዶች አያወጣም።

ሁለተኛ፥ እግዚአብሔር አብራም ፍጹም መሆን እንደነበረበት ተናግሯል። ይህ ግን እግዚአብሔር አብራምን ኃጢአት ያልነካው እንደሚሆን ይጠብቅ ነበር ማለት አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፍጹም፥ ወይም ቅዱስ መሆን ማለት፥ ሕይወቱን ለእግዚአብሔር ክብር የሚኖር በሳል ሰው መሆን ማለት ነው። ይህ ሰው ኃጢአት ወደ ሕይወቱ

ቢመጣ፥ ወዲያውኑ ኃጢአቱን ይናዘዛል። የዚህ ዓይነቱ ሕይወት ትኩረት በግብረ-ገባዊ ጽድቅ ላይ ሆኖ በእግዚአብሔርና በሌሎች ሰዎች በማይነቀፍበትና በምግባረ-ብልሹነቱም ወቀሳ በማይሰነዘርበት ሁኔታ መኖር ማለት ነው።

18ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) በቤተ ክርስቲያንህ ፍጹማን ተብለው ሊጠሩ እንደሚችሉ የምትተማመንባቸውን ያንዳንድ ሰዎች ስም ግለጽ።

ለ) የእነርሱን ሕይወት ከሌሎች ክርስቲያኖች የሚለየው ምንድነው?

እግዚአብሔር ለአራተኛ ጊዜ ቃል ኪዳኑን ለአብራም አጽንቶለታል። አብራም እግዚአብሔርን በሕይወቱ ውስጥ ተቀዳሚውን ሥፍራ የሚሰጠው ከሆነ፥ እግዚአብሔር ሁለት ነገሮችን ተስፋ ገብቶለታል። በመጀመሪያ፥ እግዝኢአብሔር ከአብራም ታላቅ ሕዝብ እንደሚወጣ ተናግሯል። ይህንንም ለማረጋገጥ፥ እግዚአብሔር የአብራምን ስም ወደ አብርሃም ለወጠ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፥ የስም መለወጥ፥ አዲስ ጅማሬንና ከእግዚአብሔር ጋር የነበረንም ግንኙነት መለወጥ ያመለክታል። (ለምሳሌ ያዕቆብ እስራኤል ተብሏል፤ ስምዖንም ጴጥሮስ ተብሎ ተጠርቷል)።

አብራም ማለት «ታላቅ አባት» ማለት ነው። ይህ የአባቱ የታራ ነጸብራቅና አብራም ትልቅ ስምና የቤተሰብ ሐረግ የነበረው ሰው ልጅ መሆኑን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። አንዳንዶች ደግሞ ይህ ስም እግዚአብሔር ለአብራም ታላቅ አባት መሆኑን ያመለክታል ይላሉ። አብርሃም የሚለው ስም በዕብራይስጥ «የብዙ ሕዝብ አባት» ማለት ሲሆን፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ታላቅ ሕዝብ እንደሚወጣ ለሰጠው ተስፋ ምልክት ሆኖ የተሰጠ ነበር። እዚህ ላይ ከልብ ልናጤነው የሚገባው፥ አብርሃም ከሦራ የተወለደ አንድም ልጅ ሳይኖረውና ከአጋርም እንኳ የወለደው አንድ ልጅ ብቻ ሆኖ ሳለ፥ ሰዎች ሁሉ «የብዙ ሕዝብ አባት» ብለው እንዲጠሩት ለግዘዝ ያበቃውን የእምነቱን ፅናት ነው።

እግዚአብሔር ከአብርሃም የተለያዩ ሕዝቦችን ለማፍራት ተስፋ ሰጠ።

19ኛ ጥያቄ፤ - ይህ የተፈጸመው እንዴት ነበር?

ከአብርሃም ከተገኙት ሕዝቦች አንዱ የእስማኤል ልጆች የሆኑት ዐረቦች ነበሩ። እንደዚሁም ከዔሳው የተገኙት ኤዶማውያንና ሌሎችም ከአብርሃም እንደሚመጡ ተነግሮ ነበር። ከሁሉም በላይ የሆነው ግን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚወለድበት የእስራኤል ሕዝብ ነበር።

እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን በደገመበት በዚህ ወቅት፥ በሁለት አበይት ነገሮች ላይ አትኩሮአል። በመጀመሪያ፥ ቃል ኪዳኑ የዘላለም ቃል ኪዳን እንደሚሆን ተናግሯል። የአብርሃም ልጆች የሆኑት እስራኤላውያን ከእግዚአብሔር ጋር እግዚአብሔር ደግሞ ከእነርሱ ጋር፥ በዘመናት ሁሉ የተለየ ግንኙነት ይኖራቸዋል። ይህ ማለት ደግሞ እያንዳንዱ እስራኤላዊ ደኅንነት የሚያስገኝ ግንኙነት በቀጥታ ከእግዚአብሔር ጋር ይኖረዋል ማለት አልነበረም። አብርሃም እንዳደረገው በእግዚአብሔር ፊት የተመላለሰ እያንዳንዱ እስራኤላዊ፥ አብርሃም የነበረውን የተለየ ግንኙነት ከእግዚአብሔር ጋር ይቀጥላል ማለት እንጂ፥ የማይታዘዝ እስራኤላዊ በእግዚአብሔርና በእርሱ መካከል የነበረውን ቃል ኪዳን ያፈረሰ ስለሚሆን፥ ከቃል ኪዳኑ ውጭ የወጣና ያልዳነ ይሆናል።

20ኛ ጥያቄ፤ -ይህ ዛሬ ከክርስቲያን ደኅንነት ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

ዛሬ ይህ ቃል ኪዳን ከእኛ ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ምሁራን ይከራከራሉ። አንዳንዶች በኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትና በሐዋርያት ሥራ በተጀመረው የቤተ ክርስቲያን ዘመን፥ አይሁዶች ኢየሱስ ክርስቶስን መሢሐቸው አድርገው ስላልተቀበሉት፥ ቃል ኪዳኑ ፈርሶአል ይላሉ። አሁን እግዚአብሔር በሥጋ የአብርሃም ልጆች ከሆኑት ከእስራኤላውያን ጋር የተለየ ግንኙነት የለውም። ይልቁንም እውነተኞቹ የአብርሃም ልጆች፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን፥ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ያላቸውና የዳኑ ናቸው ይላሉ። ለእስራኤል ሕዝብ የተሰጡ ልዩ የተስፋ ቃሎች ሁሉ (እንደ ከነዓን ምድር ተስፋ ያሉ) በቀጥታ

የምንረዳቸው ሳይሆኑ፥ ዳሩ ግን ለክርስቲያን ለተሰጠው የመንግሥተ ሰማይ ተስፋ ተምሳሌቶች ናቸው ይላሉ (ገላ. 3፡7-9፤ ሮሜ 4፡11-16)።

ሌሎች ምሁራን ደግሞ፥ እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ግዴታ የሌለው የተስፋ ቃል ገብቷል ይላሉ። ይኸውም ቃል ኪዳኑ ወደ እስራኤላውያን እንጂ፥ የአብርሃም የመንፈሳዊ ልጆች ወደ ሆኑት ክርስቲያኖች በቀጥታ አያመለክትም ባዮች ናቸው። ምንም እንኳ የእስራኤል ሕዝብ ካለማመን የተነሣ ቢቀጣና ለጊዜውም ገለል ቢደረግ፥ እግዚአብሔር አሁንም ለሥጋዊ የእስራኤል ልጆች የተለየ እቅድ አለው። የከነዓንን ምድር ሙሉ በሙሉ የሚወርሱበትና ኢየሱስ ክርስቶስም በላያቸው የሚነግሥበት ጊዜ እየመጣ ነው። የቤተ ክርስቲያን መመሥረት ግለት፥ የእስራኤል ሕዝብ ከእንግዲህ በእግዚአብሔር አይከበርም ግለት አይደለም (ሮሜ 9-11)።

21ኛ ጥያቄ፤ - አንተስ ከእነዚህ አመለካከቶች የትኛውን ትደግፋለህ? ለምን?

ምንም እንኳ ክርስቲያኖች እስከ ጌታ ምጽአት ድረስ በዚህ ጉዳይ ላይ የማይስማሙ ቢሆንም፥ እግዚአብሔር የዘላለም ቃል ኪዳንን የሰጠው አብርሃምን ለማታለል አይደለም። ይህም ቃል ኪዳን፥ ዘሩ በሥጋ ትውልዶች እንዲተካና እንዲኖሩ ነው። ሰው የአብርሃም ሥጋዊ ልጆች የሆኑት እስራኤላውያን በታሪክ ውስጥ ስለሚኖራቸው ሥፍራ ያለው መረዳት፥ በዘመናት መጨረሻ ስለሚገኘው የእግዚአብሔር እቅድ ያለውን መረዳት ይወስነዋል ብሎ ማለፉ ይመረጣል።

እግዚአብሔር ከአብርሃም ትልቅ ሕዝብ እንደሚያወጣ ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን የከነዓንን ምድር በሙሉ ለአብርሃም እንደሚሰጥም የተስፋ ቃል ገብቶለታል። ምንም እንኳ ዘወትር እንደ መጻተኛ ሆኖ ቢኖርም፥ አንድ ቀን የከነዓን ምድር የልጆቹ ርስት ትሆን ነበር። እንዲሁም እግዚአብሔር፥ ይህ ማከተሚያ የሌለው የዘላለም ቃል ኪዳን እንደሚሆንም ተናግሯል።

2. የቃል ኪዳኑ ምልክት የሆነው ግርዘት (17፡9-14)

ምንም እንኳ በእግዚአብሔርና በአብርሃም መካከል የተደረገው ቃል ኪዳን ቅድመ-ሁኔታ የሌለበት ቢሆንም፥ እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዘሮቹ ውጫዊ የቃል ኪዳን ምልክት ሰጥቶአቸዋል። ይህም የወንድ ልጅ የግርዘት ምልክት ነበር።

22ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) ብዙ ኢትዮጵያውያን የሚገረዙት ለምንድነው?

ለ) ወደ አንድ የኦርቶዶክስ ክርስቲያን ዘንድ ጎራ በልና የመገረዛቸው ዓላማ ምን እንደሆነ ጠይቅ።

ሐ) ብዙ ኢትዮጵያውያን ሴቶችንም ጨምረው የሚገርዙት ለምንድነው?

መ) ዛሬ ግርዘት አስፈላጊ ነውን? ለምን?

ሠ) ካልሆነ፥ ሰዎች ለምን ይገረዛሉ?

በብሉይ ኪዳን ግርዘት አይሁዶች በእግዚአብሔርና በአብርሃም መካከል ለተደረገው ቃል ኪዳን ተገዢዎች የመሆን ፈቅደኛነታቸውን የሚያመለክት ውጫዊ ምልክት ነበር። ዳሩ ግን፥ ይህ ለአይሁዶች ብቻ እንዳልነበረ አስተውል። በአይሁድ ሕዝብ መካከል ይኖሩ የነበሩት ግናቸውም ሕዝብ፥ በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል በተደረገው ቃል ኪዳን ሥር ለመኖር መለያ የሚሆናቸው ምልክት ነበር። ምንም እንኳ እስማኤል በተስፋ ቃል የተወለደ ልጅ ባይሆንም፥ እርሱም በቃል ኪዳኑ ሥር፥ በአብርሃም ቤተሰብ ውስጥ ይኖር ስለ ነበረ፥ ተገርዞአል። እንደዚሁም አሕዛብ ቢሆኑ እንኳ፥ በአብርሃም ቤት ውስጥ የነበሩት ወንዶች ሁሉ መገረዝ ነበረባቸው። በግርዘት፥ አብርሃምና ትውልዶቹ በእግዚአብሔር ፊት መሐላ እየፈጸሙ ነበር። እግዚአብሔርን ብቻ ለማገልገል ቃል እየገቡ ነበር። የልጃቸውን ሸለፈት መገረዝ ማለት፥ «በእምነትና በተዛዥነት ለእግዚአብሔር ታማኝ ባልሆን፥ እኔው ሸለፈቴን እንደ ቆረጥሁ ሁሉ፥ የእግዚአብሔር ሰይፍ እኔንና ትውልዶቼን ይቁረጠን» ማለት ነበር።

ስለ ግርዘት ልናስታውሳቸው የሚገቡ አንዳንድ አስፈላጊ ነገሮች አሉ፡ - በመጀመሪያ፥ ግርዘት በዚህ ወቅት ለዓለም አዲስ አልነበረም፤ ይገረዙ የነበሩትም አይሁዶች ብቻ አልነበሩም። ግብፃውያንና ሌሎች

የበርካታ ባሕል ሕዝቦችም ለተለያዩ ምክንያቶች ይገረዙ ነበር። በአይሁዶችና የግርዘትን ልምምድ ያደርጉ በነበሩት በሌሎች ሕዝቦች መካከል የነበረው ልዩነት የሚያመለክተው ነገር ነበር። ግዝረት ለአይሁዶች የተሰጠበት ልዩ ምክንያት የአብርሃም ልጆች እንደመሆናቸው፥ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች ለማስታወስና ለቃል ኪዳኑ በታማኝነት እንዲኖሩ ለማድረግ ነበር። የአባታቸውን የአብርሃም አምላክ እርሱ በነበረው ዓይነት እምነት ለመከተል የተሰጠ፥ ልዩ ሕዝቦች የመሆናቸው ምልክት ነበር።

23ኛ ጥያቄ፤ - ዘጸ. 30፡6ን አንብብ።

ሀ) ሙሴ በዚህ ጥቅስ ውስጥ ግርዘት እንደሚያሻው የሚናገረው ስለ ምንድነው?

ለ) ይህ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል የተደረገውና የታየው እንዴት ይመስልሃል?

ሁለተኛ፥ እግዚአብሔር የግርዘትን ሥርዓት የመረጠው፥ ለእግዚአብሔር ሕዝብ የንጽሕናን አስፈላጊነት ስለሚያመለክት ነበር። የሰው ሽለፈት ተቆርጦ እንደሚወገድ ሁሉ፥ እነርሱም ከፉውን የዓለም ልምምድ ሁሉ አስወግደው፥ ለእግዚአብሔር በንጽሕና መኖር ነበረባቸው [መዝ. (118)፡10፤ ሮሜ 2፡28-29]። እውነተኛው የቃል ኪዳኑ ምልክት ልቡን የገረዘ፥ ለእግዚአብሔር በታዛዥነት የኖረና በኑሮ መመሪያው ሁሉ በእግዚአብሔር ትዕዛዛት ውስጥ የሚገኝ ሰው ነበር። እግዚአብሔር ለግርዘት ምልክት ኃፍረተ - ሥጋን መምረጡ አስገራሚ ነገር ነው። ምናልባት ብዙውን ጊዜ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ወደ እድፈት የሚያመራው ይህ ኃፍረተ-ሥጋው መሆኑን ስለሚያውቅ ይሆናል። እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያንን የጸታ አካሎቻቸው እርሱን እንዲያከብሩ ለማስተማር ይፈልጋል። የጸታ ግንኙነት መፈጸም ያለበት በጋብቻ ውስጥ ብቻ ሲሆን፥ የተቀደሱ ልጆችን በማፍራቱ አገልግሎት ላይ መዋል ነበረበት (ሚል. 2፡10-17)።

24ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) ይህ ትምህርት ዛሬ ለቤተ ክርስቲያን ሊያገለግል የሚችለው እንዴት ነው?

ለ) በእግኖች ሕይወት ውስጥ፥ የጾታ ግንኙነትን ንጽሕና መጠበቅ በጣም አስቸጋሪ የሚሆነው ለምንድነው?

ሦስተኛ፥ ግርዘት አንድን ሰው የእግዚአብሔር ልጅ የማድረግ ዋስትና አልነበረውም። የቃል ኪዳኑ ምልክት ትርጉም እንዲኖረው ከተፈለገ፥ ከእምነት ጋር መዋሐድ ነበረበት። ግርዘት ብቻውን ባዶ ሥርዓት ነበር። እስማኤልና ዔሳው ሁለቱም የተገረዙ ቢሆኑም፥ አንዳቸውም የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላት አልነበሩም። እንዲያውም በጓላ ላይ የእግዚአብሔር ጠላቶች ሆነዋል። የግርዘት ምልክት ኃይል ያለው በግርዘቱ ተግባር ላይ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን በተግባሩ ትርጉም ላይ ነው (ሌሎችም ባሕሎች ተጠቅመውበታል)። ይኸውም አይሁዶች ራሳቸውን ለእግዚአብሔር በማስገዛት፥ በቃል ኪዳኑ ሥር፥ በታዛዥነትና በእምነት ለመኖር የመፍቀዳቸው ምልክት ነው።

አልገረዝም ያለ ግንም ቢሆን «ከሕዝቡ ተለይቶ መጥፋት» ነበረበት። ራሳቸውን ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ጋር ለማስተባበር ያልፈለጉ ሰዎች፥ ሌላ ምንም የበረከት በር አልነበራቸውም። በእግዚአብሔር ፊት በማመፅ ስለሚኖሩ መቀጣት ነበረባቸው። ተለይቶ መጥፋት ሦስት ትርጉሞች ሊኖረው ይችላል። በመጀመሪያ፥ እስራኤላውያን ያንን ሰው ከህብረተሰባቸው መካከል ማስወጣት ነበረባቸው። ሁለተኛ፥ የማይገረዘውን ሰው መግደል እንደነበረባቸው የሚናገር ሊሆን ይችላል። ሦስተኛ፥ እግዚአብሔር ለአብርሃም ከሰጣቸው የተስፋ ቃሎች ያንን ሰው እንዳገለለውና በራሱም ጊዜ እንደሚቀጣው የሚገልጽ ሊሆን ይችላል።

25ኛ ጥያቄ፤ - ክርስቲያኖች መገረዝ የሚያስፈልጋቸው ይመስልሃል? ለምን?

መመለስ የሚያሻን ጥያቄ «ዛሬ ግርዘት ምን ጥቅም አለው?» የሚለውን ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ አሁንም በርካታ ሰዎች ግርዘትን ይፈጽማሉ። ለአርቶዶክስ ክርስቲያኖች፥ ይህ ሕፃናት የእግዚአብሔር ቤተሰብ ወደ መሆን መምጣታቸውን የሚያመለክት ሥርዓት ነው። ተምሳሌታቸውንም የሚወስዱት ከብሉይ ኪዳን ውስጥ ነው። ቢሆንም፥ ሥጋዊ የግርዘት ተግባር፥ ከእንግዲህ በእግዚአብሔር ፊት ምንም ዋጋ

እንደ ሌለው፥ ከአዲስ ኪዳን ውስጥ በግልጽ ይታያል። ሰውየው ቢገረዝ ወይም ባይገረዝ ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረውን ግንኙነት አየለውጠውም (ሮሜ 2፡25-29፤ 1ኛ ቆሮ 7፡19 ተመልከት)። ባሁኑ ጊዜ መገረዝ ወይም አለ መገረዝ መንፈሳዊ ጠቀሜታ የሌለው ባሕላዊ ልምምድ ብቻ ነው። እግዚአብሔር የሚያተኩረው አንድ ክርስቲያን ከዓለምና ከኃጢአት፥ በእግዚአብሔር ፊት ወዳለው የመታዘዝ ሕይወት በሚመለስበት የልብ ግርዘት ላይ ነው። ማንኛውም ሥጋዊ ተግባር፥ ጥምቀትም እንኳ ቢሆን፥ እኛ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላት እንድንሆን ዋስትና አይሰጠንም። ከእምነት ጋር እስካልተባበረ ጊዜ ድረስ ከንቱ ነው።

26ኛ ጥያቄ፤ - ጥቅም እንዲኖራቸው ከተፈለገ ከእምነት ጋር መተባበር ያለባቸውን አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ልምምዶች ዘርዝር።

የግርዘት ዓላማ ለአይሁዶች እግዚአብሔር በአብርሃም በኩል ከእነርሱ ጋር ለገባው ቃል ኪዳን የማስታወሻ ምልክት እንዲሆን ነበር። ለክርስቲያኖች፥ በአንዳንድ በኩል ከግርዘት ጋር የሚመሳሰሉ ሁለት ሌሎች ምልክቶች አሉ። በመጀመሪያ፥ የጥምቀት ምልክት አለ። ክርስቲያኖች እንዲጠመቁ ታዝዘዋል። ጥምቀት ክርስቲያኑ ለቀደመው የሕይወት መንገዱ ሁሉ ከክርስቶስ ጋር እንደ ሞተና በአዲስ ሕይወት ለእግዚአብሔር ለመታዘዝ ከክርስቶስ ጋር እንደተነሣ፥ የሚያሳይ ምልክት ወይም ምሳሌ ነው። በተለይም ለማያምኑ ሰዎች፥ የተጠመቀው ሰው ለእግዚአብሔር ለመኖር እንደ ተሰጠ የሚያሳይ ምልክት ነው። ይሁን እንጂ፥ ሥጋዊ የጥምቀት ተግባር ማንንም ሊያድን አይችልም። የጥምቀት ተግባር እምነትን ሊከተልና ከእምነትም ጋር ሊተባበር ይገባዋል። ክርስቲያኖች የጥምቀት ተግባር ለምን እንደሚፈጸም እስካልተገነዘቡ ድረስ፥ የሚሰጣቸው ምንም መንፈሳዊ ጠቀሜታ የለውም። የሕፃናት ጥምቀት መንፈሳዊ ጠቀሜታ የማይሰጥበት አንዱ ምክንያት ይኼ ነው። እንዲሁም ክርስቲያኖች የጥምቀትን ሥርዓት የማይፈጽሙ ከሆነ ስሕተት ነው። ምክንያቱም ይህ በማያምነው ዓለም ፊት ለእግዚአብሔር ያላቸውን እምነትና ታማኝነት እንዲገልጹ በእግዚአብሔር የተሰጣቸው ምልክት ነው። ጥምቀት ውስጣዊውን

ለውጥ የሚያሳይ ውጫዊ ምልክት ሲሆን፥ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን አዲስ የሕይወት ጉዞ ለሚያምኑና ለማያምኑ ሰዎች የሚመሰክር ነው።

27ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) በቤተ ክርስቲያንህ ብዙዎቹ ክርስቲያኖች ተጠምቀዋልን?

ለ) አንዳንድ ክርስቲያኖች ለመጠመቅ የማይፈልጉት ለምንድነው?

ሐ) የጥምቀት ዓላማ ምን እንደሆነና ዓላማውንም ሰዎችን ከማጥመቋ በፊት ቤተ ክርስቲያንህ እንዴት እንደምታስረዳቸው በአንድ አጭር አንቀጽ ግለጽ።

28ኛ ጥያቄ፤ - 1ኛ ቆሮ. 11፡23-26 አንብብ። የጌታን እራት መውሰድ የምን ምልክት ነው?

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁለተኛው ምልክት የጌታ እራት ነው። ምንም እንኳ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ጎብስቱንና ወይኑን መውሰድ የኃጢአት ይቅርታ እንደሚያስገኝ ቢያስተምሩም፥ ይህ ስሕተት ነው። ይህ የጌታ እራት ምልክት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በክርስቲያኑ ፈንታ መሞቱን ለሰዎች ለማስታወስ («ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉ») የተሰጠ ምልክት ነው። ይህ ምልክት ለክርስቲያኑ መንፈሳዊ ጠቀሜታ ሊሰጥ የሚችለው፥ እምነት፥ ንስሐ መግባትና ለእግዚአብሔር መታዘዝ ሲኖር ብቻ ነው። እንደ ግርዘት ሁሉ፥ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለውን ቃል ኪዳን ያመለክታል። በኢየሱስ ሞት ላይ የተመሠረተው የአዲስ ኪዳን ምልክት ነው።

29ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) የጌታን እራት መውሰድ ለእምነትህ ጠቃሚ የሆነው እንዴት ነው?

ለ) አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት፥ የጌታን እራት የቤተ ክርስቲያን አባላት ብቻ እንዲወስዱ የሚያደርጉት ለምድነው?

ሐ) ይህ ትክክል ነው ወይስ አይደለም? አብራራ።

የሚገረዘው ወንድ ልጅ ብቻ እንደነበረም መረዳት አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ የሴትን ግርዘት አይደግፍም። ሴትን ስለሚጎዳ፥ ይህ አደገኛ እና አላስፈላጊ፥ ብሎም የተሳሳተ ባሕላዊ ልምምድ ነው። የሴቷን የወሲብ ፍላጎት መቀነስ ብቻ ሳይሆን፥ በተለይም በወሊድ ጊዜ አደገኛ ነው። ከሴት ግርዘት የተነሣ በሚፈጠረው ችግር ሳቢያ በየዓመቱ ብዙ ሴቶች ይሞታሉ።

3. ከሣራ ልጅ እንደሚወለድ የተሰጠ የተስፋ ቃል (17፡15-22)።

አብርሃምና ሣራ እግዚአብሔር ልጅ እንደሚሰጣቸው የገባላቸውን የተስፋ ቃል በሰብዓዊ ጥበብ ለማሳካት ሞክረዋል። በውጤቱም እስማኤል ተወልዷል። ዳሩ ግን እግዚአብሔር በተፈጥሮአዊ ዘይቤ የተወለደውን ልጅ ለማክበር አልፈለገም ነበር። እግዚአብሔር እንደ ተስፋ ቃሉ በተአምር የሚወለደው ይስሐቅ የአብርሃም የተስፋ ቃሎች ወራሽ እንዲሆን ፈለገ። ስለሆነም፥ ሣራ ለአብርሃም ልጅ እንደምትወልድ እግዚአብሔር የተስፋ ቃል ሰጠ።

ከዚህ ቀደም እግዚአብሔር የአብራምን ስም አብርሃም ብሎ የለወጠው ሲሆን፥ በዚህ ጊዜ የሦራን ስም ሣራ ብሎ ቀይሯል። በስሞቹ ትርጉም ውስጥ ብዙ ልዩነቶች አልነበሩም። ሦራና ሣር ሁለቱም «ልዕልት» ወይም «ንግሥት» የሚል ትርጉም ይይዛሉ። ዳሩ ግን የስሟ መለወጥ ሣራም አዲስ በሆነ ግንኙነት ሐሴት እንደምታደርግ የሚያመለክት ነበር። ከእርሱ ነገሥታት የሚወጡበትን ልጅ ትወልዳለች። «ልዕልቷ» ነገሥታትን ትወልድ ነበር። የነገሥታት ንጉሥ የሆነው፥ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚወለደው በልጅዋ ልጆች በኩል ነበር።

ይህ ለአብርሃም ለማመን የሚያስቸግር ነበር። የእምነቱን አናሳነት በሚያመለክቱ ሁለት መንገዶች ምላሽ ሰጥቷል። አብርሃም እንደ እኛው ሰው ነበር። ምንም እንኳ እግዚአብሔርን ቢያመልክም፥ የጥርጣሬና ያለማመን ጊዜያት ነበሩት። በመጀመሪያ፥ አብራም የእርሱንና የሣራን በሥጋዊ ሁኔታ ልጅ የመውለድ ብቃት ስለተጠራጠረ ሳቀ። እውነትም ይህ በሰው አመለካከት የማይቻል ነገር ነበር። በዚህ ጊዜ አብርሃም ወደ 100 ዓመት አካባቢ ሲሆን፥ ሣራም የ90 ዓመት አሮጊት ነበረች።

ሥጋዊ ብቃታቸው፥ በተለይም የሣራ እንደሙት የሚቆጠር ነበር (ዕብ. 11፡11-12 ተመልከት)።

ሁለተኛ፥ አብርሃም እስማኤል የተሰፋው ልጅ እንዲሆን ጠየቀ። ለ13 ዓመታት አብሮት ስለ ነበረ፥ አብራም እስማኤልን እንደ ወደደው አይጠረጠርም። እንዲሁም ደግሞ ብቸኛ ልጁ ነበር። እስማኤል የበኩር ልጅ ነበር። ለዚህ ነው ዛሬ ሙስሊሞች የአብርሃም እውነተኛው ልጅና የተሰፋ ቃሎቹ ወራሽ ታላቁ ልጅ እስማኤል ነው የሚሉት። ሙስሊሞች የእግዚአብሔር የበረከት ተቀባዮች ራሳቸው እንጂ፥ አይሁዶች እንዳልሆኑ የሚያስቡትም ለዚህ ነው።

እግዚአብሔር የአብርሃም ልጅ የሆነውን እስማኤልን እንደሚባርከው የተሰፋ ቃል ገብቷል። ዘሩ በከፍተኛ ደረጃ ይባዛል። ልክ ያዕቆብ የ12ቱ የእስራኤል ነገዶች አባት እንደ ነበረ ሁሉ፥ የ12 አለቆች አባት ይሆናል። እስማኤላውያን ወይም ዐረቦች ታላቅ ሕዝብ ይሆናሉ። ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝብ አይሆኑም ነበር። ያ የሚሆነው ለአብርሃምና ለሣራ የተሰፋ ልጅ መሆን ነበረበት። አብርሃም በእግዚአብሔር ችሎታ ላይ እንደ ሳቀ ሁሉ፥ ይህን ጥርጣሬውን ያስታውሰው ዘንድ የእርሱንና የሣራን ልጅ ይስሐቅ (ሳቅ) ብሎ ሰየመው። ከአብርሃም ጋር የተደረገው ቃል ኪዳን ዘላለማዊ የተሰፋ ቃሎች የሚሰጡት ለይስሐቅ ነበር።

30ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) እግዚአብሔር እስማኤልን የተሰፋው ልጅ እንዳይሆን የከለከለው ለምን ይመስልሃል?

ለ) ከዚህ ምን እንግራለን?

4. አብርሃም በቤቱ ውስት የነበሩትን ወንዶች ሁሉ በታዛዥነት ገረዘ (16፡23-27)።

እግዚአብሔር ልጅ የመስጠቱን ተስፋ ካደሰለት በኋላ፥ ከአብርሃም ተለየ። አብርሃም የእግዚአብሔርን ቃል አልተጠራጠረም ነበር። በቤቱ ውስጥ የነበሩትን ወንዶች፥ ባሪያዎችንም ሳይቀር በፍጥነት ገረዘ። በዚህ ጊዜ አብርሃም 99 ዓመቱ ሲሆን፥ እስማኤል 13 ዓመቱ ነበር። አብርሃም እግዚአብሔርን በመታዘዝ የቃል ኪዳኑን ምልክት ለራሱ ግላዊ አደረገ። አብርሃም እምነቱን በመታዘዝ አሳየ።

ክርስቲያኖች ሁሉ እግዚአብሔር ለእነርሱ በሰጣቸው በርካታ የተለያዩ የተሰፋ ቃሎች ይደሰታሉ። እኛም ከእግዚአብሔር ጋር ዘላለማዊ ቃል ኪዳን አለን - አዲስ ኪዳን። ይሁን እንጂ፥ ቃል ኪዳኑን፥ የምንቀበል ከሆን፥ ግዴታዎች አሉብን። ቃል ኪዳኑን ለመቀበል በኢየሱስ ክርስቶስ የማመን ግዴታ አለብን። በእግዚአብሔር ላይ ያለንንም እምነት ለትዕዛዛቱ በመታዘዝ ማሳየት አለብን። ለእግዚአብሔር ታማኞች መሆን አለብን። በአፋችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስለምናምን፥ ወይም ቤተሰቦቻችን ክርስቲያኖች ስለሆኑ፥ የዝላለምን ሕይወት እናገኛለን ማለት አይደለም። እግዚአብሔር የእምነታችንን እውነተኛነት በማሳየት እንድንገዛለትና እንድንታዘዘው ይፈልጋል።

31ኛ ጥያቄ፤ - በኢየሱስ ያለህን እምነት እውነተኛነት በየዕለቱ በሕይወትህ የምታሳይባቸውን መንገዶች ዘርዝር።

ሦስተኛ ቀን፡ - ዘፍጥረት 18

እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር በኡሪት ዘፍጥረት 17 ከተገናኘ በኋላ ብዙ ወራት ሳያልፍ እንደገና አብርሃምን ለመነብኘት ተመለሰ። ይህ ጉብኝት ሁለት አበይት ዓላማዎች ነበሩት። በመጀመሪያ፥ ልጅ የሚያገኙበት ጊዜ በመጨረሻ ላይ መድረሱን፥ እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለሣራ ለመንገር ሲሆን፥

ሁለተኛው፥ ደግሞ እግዚአብሔር በሰዶምና ገሞራ ላይ የሚመጣውን ጥፋት ለአብርሃም ለመንገር ነበር። በእነዚህ ሁለት አጋጣሚዎች የእግዚአብሔርን ሁለት ልዩ ባሕሪያት እንመለከታለን። ለመጀመሪያ፥ እግዚአብሔርን ተአምር እንደሚሠራ አምላክ ሆኖ እንመለከታለን። ሊሠራው የሚያስቸግረው ነገር ምንም የለም። ሁለተኛ፥ እግዚአብሔር ፍትሕ እንደሚሰጥ አምላክ ሆኖ እንመለከታለን። እግዚአብሔር ጻድቁን አይቀጣውም፤ ዳሩ ግን ኃጢአተኛውን ይቀጣዋል።

32ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) ስለ እግዚአብሔር እነዚህን ሁለት ነገሮች ማስታወስ የሚያስፈልገው ለምንድነው?

ለ) እነዚህን እውነቶች ወደ መዘንጋቱ የምናዘነብልባቸውን ሁኔታዎች ግለጽ።

33ኛ ጥያቄ፤ - ዘፍጥረት 18ን አንብብ። ሀ) አብርሃምን ለመጎብኘት ስንት ሰዎች መጡ።

ለ) እነማን ይመስሉሃል? (18፡16፤ 19፡1 ተመልከት)

ሐ) እግዚአብሔር ለአብርሃም ምን የተስፋ ቃል ሰጠው? (ቁ. 10)።

መ) የሣራ ምላሽ ምን ነበር?

ሠ) እግዚአብሔር ለሣራ የተናገረውና ኃይሉን የሚያመለክት ነገር ምን ነበር? (ቁ. 14)

ረ) እግዚአብሔር በሰዶም ላይ የነበረውን ዓላማ ለአብርሃም መግለጽ እንዳለበት የተናገረው ለምንድነው? (ቁ. 17-19)።

ሰ) እግዚአብሔር ወደ ሰዶም ለምን እንደሚሄድ ምን ሲል ተናገረ? ይህስ ምን ማለት ነው?

ሸ) የሰዶምን የጥፋት ወሬ በሰማ ጊዜ አብርሃም የተጨነቀው ለምን ነበር?

ቀ) እግዚአብሔር የተማመነበት የእግዚአብሔር ባሕርይ ምን ነበር? (ቁ. 25)

በ) አብርሃም በእግዚአብሔር ፊት የግለደባቸውን የተለያዩ የሰዎች ቁጥሮች ዘርዝር።

1. እግዚአብሔር ለአብርሃም ልጅ ለመስጠት የተስፋ ቃል ይገባል (18፡1-15)።

አንድ ቀን አብርሃም ከድንኳኑ ወጣ ብሎ በሚገኝ የዛፍ ጥላ ሥር ተቀምጦ ነበር። ጊዜው ሞቃት ስለ ነበር፥ ዕረፍት እያደረገ ነበር። ወዲያው ቀና አለና ሦስት ሰዎች ከአጠገቡ ቆመው ተመለከተ። አብርሃም እነዚህ ሦስት ሰዎች እነማን እንደ ነበሩ ያወቃቸው ስለ መሆኑ አጠራጣሪ ነው። ምናልባት በዚያ የሚያልፉ የተከበሩ መንገደኞች

ሳይመስሉት አይቀርም። ዳሩ ግን፥ እንደ መልካም እንግዳ ተቀባይ፥ አብርሃም ወደ ድንኳኑ ጋበዛቸውና ምግብ አቀረበላቸው።

እነዚህ ሦስት ሰዎች እነማን ነበሩ? እንግዶች በአካባቢው የተለመዱ ዓይነት ሰዎች እንዳልሆኑ ከታሪኩ ውስጥ በግልጽ ይታያል። ከሰዎቹ አንዱ ጌታ እንደ ነበረ እናውቃለን (ዘፍ. 18፡1፤ 16-17 ተመልከት)። ብዙ ክርስቲያናች ይህ ቀደም ብለን የተነጋገርንበት «የእግዚአብሔር መልአክ» እንደሆነ ያስባሉ። ይህም የሰውን ሥጋ ከመልበሱ በፊት፥ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰዎች የሚገለጽበት የብሉይ ኪዳን ሁኔታ ነበር። ሌሎች ሁለቱ ሰዎች ግን መላእክት እንደ ነበሩ በነገው ትምህርታችን እንመለከታለን።

አዲስ ኪዳን ይህንን ታሪክ መልካም የእንግዳ ተቀባይነት ምሳሌ አድርጎ ይጠቀምበታል (ዕብ. 13፡2 ተመልከት)። ምንም እንኳ አብርሃም በመጀመሪያ ሦስቱ ሰዎች እነማን እንደ ነበሩ ላያውቅ ቢችልም፥ ቤቱን ለእነርሱ ክፍት አድርጎ ተቀብሎአቸዋል። እንከብካቤም አድርጎላቸዋል። እኛም እንደዚሁ፥ ማንነታቸውን ላናውቅ ብንችልም፥ ሌሎችን እንግድነት እንድንቀበልና እንድንንከባከባቸው እግዚአብሔር ይጠብቅብናል።

34ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) ለክርስቲያኖች፥ በተለይም ለክርስቲያን መሪዎች እንግዳ ተቀባይነት የሚያስፈልጋቸው ለምንድነው?

ለ) ይህ ባመዛኙ በክርስቲያን መሪዎች ይደረጋል ወይስ አይደረግም? አብራራ።

በዚህ ጉብኝቱ እግዚአብሔር እግረ-መንገዱን ከአብርሃም ጋር የገባውን የቃል ኪዳን ተስፋዎች እንደገና እያደሰ ነበር ለማለት ይቻላል። የጥንት ሰዎች ቃል-ኪዳናቸውን ከሚያጸኑባቸው መንገዶች አንዱ አብሮ ግዕድ በመቁረስ ነበር። ይህም በአብርሃምና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው ህብረት ምን ያህል እንደተቀራረበ የሚያሳይ ሥዕላዊ ገለጻ ነበር። የሚያስደንቀው እውነት የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ የሆነው አምላክ፥ አብርሃም ልጅ እንደሚያገኝ በግል ለመናገር ወደ ምድር መውረዱና ከእርሱም ጋር ህብረት ማድረጉ ነው። ምላሹን ግን አስተውል።

ሦስቱ ሰዎች በምግብ ገበታ ላይ ሆነው፥ ስለ ሣራ ጠየቁት። ምናልባት በዚህ ጊዜ እነዚህ ሦስት ሰዎች ተራ ሰዎች እንዳልሆኑ መረዳት ጀምሮ ይሆናል። ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጡ መሆናቸው ቀስ በቀስ እየተከሰተለት ሄዶ ነበር። ከመላእክቱ አንዱ፥ ማለትም ጌታ፥ በምዕራፍ 17 ላይ የሰጠውን ከሣራ ልጅ የማግኘት ተስፋ አደሰ። በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ አብርሃምና ሣራ ልጅ እንደሚያገኙ ተስፋ ሰጣቸው።

በድንኳን ውስጥ ተቀምጣ የነበረችው ሣራ፥ የተነገረውን ሰማች። ባለማመንና ምናልባትም በቁጣ በልቧ ሳቀች። በሣራ ላይ ከመፍረዳችን በፊት፥ እግዚአብሔር መጀመሪያ የተሰፋ ቃል ከገባላቸው 25 ዓመታት እንደ ተቆጠሩ ልብ እንበል። እነዚያ የመጠበቅ ዓመታት ሁሉ ለእርስዋ መራራ ጊዜያት ነበሩ። ከሥጋዊ ዓይኖች ዘልቃ ለማየት አትችልም ነበር። የ90 ዓመታት አሮጊት ስለ ነበረች፥ አብርሃምና እርስዋ ልጅ ለመውለድ በሥጋዊ ሁኔታዎች በጣም እንዳረጁ ተገንዝባለች።

እግዚአብሔርም በሣራ ልብ ውስጥ የነበረውን ጥርጣሬ አወቀ። በመንፈሳዊ ሕይወቷ ለማደግ ከመቻሏ በፊት ይህ ጥርጣሬ ከውስጧ ሊወገድ እንደሚገባውም ያውቃል። እግዚአብሔር በእርሱ ላይ ስለ ሳቀች ወቀሳት። ሣራ ግን ይባስ ብላ እግዚአብሔርን ዋሸችው። ምንም እንኳ እግዚአብሔር የተሳቀበት ቢሆንና ባይታመንም፥ ልጅ የመስጠቱን ተስፋ አደሰ። የማይቻለው ለእርሱ ይቻል የል!

35ኛ ጥያቄ፤ ሀ) በሕይወትህ ወይም በቤተ ክርስቲያንህ፥ በሥጋ እንደማይቻሉ የምትገምታቸውን ወይም እግዚአብሔር ተአምር እንዲሠራ መንገድ የሚከፍቱ ሆነው ሊታዩ የሚችሉትን አንዳንድ ሁኔታዎች ዘርዝር።

ለ) ለእነዚህስ ነገሮች ያንተ ምላሽ እንዴት ነበር?

ሐ) ምላሽህ ምን መሆን ነበረበት?

የዚህ ታሪክ አቢይ ዓላማ ምንድነው? እግዚአብሔር አብርሃምና ሣራን፥ እስራኤልንና እኛ ሁላችንንም፥ ምን ያህል ኃያል እንደሆነ ለማስተማር ፈልጎ ነበር። እግዚአብሔር «በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን?» ብሏል። በእርግጥ ለዚህ ጥያቄ ምላሹ «የለም»

የሚል ነው። በሕይወታችን ውስጥ የሚያጋጥመንን አስቸጋሪ ሁኔታ በሁለት መንገዶች ለመመልከት የምንመርጥበት ጊዜ አለ። እንደሰብዓዊ አመለካከታችን፥ ሁኔታው የማይቻል ከመሰለን የመጀመሪያ ዝንባሌያችን ጥርጣሬ ነው። ሁኔታዎችን የምንመለከተው በሥጋዊ ዓይኖቻችን ብቻ ነው። ወይም ይህን አስቸጋሪ ሁኔታ በእምነት ዓይናችን የምንመለከትበት ጊዜ ይኖራል። ስለዚህ ይህ ችግር በእግዚአብሔር ለመታመንና የእርሱን ኃይል በሥራ ላይ ለማየት ድንቅ አጋጣሚ ይሆናል። ዓይኖቻችንን በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ላይ ከተከልን፥ የማይፈነቀሉ ድንጋዮች ይሆኑብንና ጥርጣሬና ተስፋ መቁረጥ ይከሰታሉ። ዳሩ ግን ዓይኖቻችንን በእግዚአብሔር ኃይልና የተስፋ ቃሉች ላይ ከተከልን፥ በታላቅ ኃይል እንዲሠራ ለመጠበቅ እንችላለን። የእምነት ሕይወት ለመምራት ከሥጋዊ ነገሮች በስቲያ እንድንመለከትና በሥጋዊ ችግሮች ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ኃይል ላይ ተመሥርተን እንድንኖር ይጠበቅብናል።

2. አብርሃም ሰዶም እንዳትጠፋ ይማጸናል (17፡16-33)።

የእምነት ሕይወት በተጨማሪም እግዚአብሔርን በማወቅ ማደግንም ይጨምራል። ጳውሎስ ለክርስቲያኖች «የክብር አባት፥ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ፥ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ» (ኤፌ. 1፡17) ይላል። አብርሃም ከእግዚአብሔር ጋር መመላለስና በእምነቱም ማደግ በጀመረ ጊዜ፥ ስለ እግዚአብሔር ያለው ዕውቀትም ጨመረ። ክርስትና ስለ እግዚአብሔር የማመን ስልቶች የሚስተዋሉበት ሳይሆን፥ ከእግዚአብሔር ጋር አዳጊ የሆነ ግንኙነት የሚዳብርበት ነው። ለዚህ ነው አብርሃም የእግዚአብሔር ወዳጅ ተብሎ የተጠራው (2 ዜና 20፡7)።

36ኛ ጥያቄ፤ - በመጀመሪያ ክርስቲያን ከሆንህበት ጊዜ አንስቶ፥ ስለ እግዚአብሔር ያለህ እውቀትና ከእርሱ ጋር የምታደርገው ግንኙነት ያደገው በምን በምን መንገዶች ነው?

ሦስቱን ሰዎች (እግዚአብሔር እና መላእክቱ) ካስተናገዳቸው በኋላ፥ አብርሃም አሸኛኘትም አደረገላቸው። ከሙት ባሕር በስተ ደቡብ ወደነበረችው ወደ ሰዶም እየሄዱ ነበር (ከመጽሐፉ በስተ ጀርባ ባለው

ካርታ ላይ ተመልከት)። እግዚአብሔርም ከአብርሃም ጋር ከነበረው ግንኙነት የተነሣ፥ ሊያደርግ ያለውን ነገር ሊነግረው ወሰነ።

እግዚአብሔር አብርሃምን እንዴት እንደገለጸው ልብ በል። በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ እግዚአብሔር ለሁላችንም፥ በተለይም ለልጆቻችን ያለውን እቅድ እንመለከታለን። እግዚአብሔር ለአብርሃም ቃል ኪዳን በመግባቱ፥ አብርሃም ታላቅ ሕዝብ እንደሚሆንና ለሰዎች ሁሉ የበረከት ምንጭ እንደሚሆን ያውቅ ነበር። ዳሩ ግን የቃል ኪዳኑን ሁለት ክፍሎች አስተውል። በመጀመሪያ፥ እግዚአብሔር አብርሃምን መረጠው። ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን ግንኙነት የጀመረው አብርሃም አልነበረም። ዳሩ ግን በምድር ላይ ይኖሩ ከነበሩት ሰዎች ሁሉ፥ እግዚአብሔር እርሱን ለተለየ ዓላማ መረጠው። እኛም እንደዚሁ በእግዚአብሔር ለተለየ ዓላማ ተመርጠናል። በደኅንነት ውስጥ የመጀመሪያው ደረጃ፥ የእኛ ጌታን መምረጥ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን እግዚአብሔር እኛን መምረጡ ነው (ሮሜ 8፡29-30 ተመልከት)። እንዲሁም አብርሃም ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን የቅርብ ግንኙነት ልብ በል። እግዚአብሔር በአብርሃም ይተማመን ነበር።

ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ምርጫ ምላሽ ሊሰጠው ይገባል። ማመንና መታዘዝ አለብን። እግዚአብሔር አብርሃምን ስለ መረጠ፥ እርሱና ልጆቹ በፍትሕና በጽድቅ እየኖሩ እግዚአብሔርን ይከተሉታል። አብርሃም ልጆቹን በእግዚአብሔር መንገድ ስለሚመራበትና ስለሚያስተምርበት ሁኔታ እግዚአብሔር የሰጠውን ትልቅ ትኩረት አስተውል። ክርስቲያን ወላጆች እንደ መሆናችን፥ የመጀመሪያው ኃላፊነታችን ልጆቻችንን ስለ እግዚአብሔር ማስተማራችንንና ለሕይወታቸውም እርሱ የሚሻውን ነገር ማመልከት ነው። እኛ ክርስቲያኖች ስለሆንን ብቻ፥ እነርሱም ክርስቲያኖች ናቸው ማለት አንችልም። እያንዳንዱ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመቀበልና ለመከተል መምረጥ አለበት። ዳሩ ግን ገና ከማለዳው በኢየሱስ ማመንና መታዘዝ ምን እንደሆነ ልናስተምራቸው ይገባል። የእምነት ጉዞ ለእግዚአብሔር የመታዘዝ ሕይወት እንድንኖርም ይጠይቅብናል። ያም መታዘዝ ሁል ጊዜም ከሌሎች ሰዎች ጋር በሚኖረን ግንኙነት ውስጥ ራሱን በጽድቅና በፍትሕ ይገልጻል።

37ኛ ጥያቄ፤ ኤፌ. 2፡10 አንብብ።

ሀ) የተፈጠርነው ለምንድነው?

ለ) እግዚአብሔር እንድንሠራቸው ከሚፈልግብን ከእነዚህ ሥራዎች አንዳንዶቹ ምንድን ናቸው?

38ኛ ጥያቄ፤ ሀ) የፍትሕና የጽድቅን ፍቺ ጻፍ።

ለ) ክርስቲያኖች እነዚህን ሁለት ባሕርያት የሚያሳዩበትን ሁኔታ ግለጽ።

ምንም እንኳ ፍትሕና ጽድቅ ሁለቱም ቃላት በጣም የሚመሳሰሉ ቢሆኑም፥ በመካከላቸው አናሳ የሆነ ልዩነት ይታያል። ጽድቅ የሚያመለክተው ከታወቀው የእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር መስማማታችንን ነው። ፍትሕ፥ በተለይም ከሌሎች ሰዎች ጋር በሚኖረን ግንኙነት ውስጥ፥ ለእግዚአብሔር መሻቶች በሚስማማ መንገድ፥ ትክክለኛ ውሳኔዎች ማድረግ ነው። እነዚህ ሁለቱም የእግዚአብሔር ልጆች መለያ ጠባዮች መሆን የሚገባቸው ሲሆን፥ ለበረከትም አስፈላጊዎች ናቸው [መዝ. (93)፡5] ።

በፍትህና በጽድቅ መኖር የሚያስፈልገን፥ እነዚህ የሰማዩ አባታችን መለያ ባሕሪያት ስለሆኑ ነው። እግዚአብሔር ጻድቅ ነው። እንዲሁም ፍትሕ አድራጊ ነው። የእግዚአብሔርን መንገዶች ለመጓዝ የማይፈልጉትን ሰዎች መቅጣትም የፍትሕ አድራጊነቱ አካል ነው። ብዙ ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን የፍቅር አምላክ ብቻ አድርገው በመመልከት ይሳሳታሉ። እግዚአብሔር ፍቅር ነው። ደግሞም እግዚአብሔር «የሚያጠፋ እሳት»ም ነው (ዕብ. 12፡29)። እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ፥ ኃጢአትን ይጠላል።

እግዚአብሔር ለአብርሃም ቅጣት ይገባቸው እንደሆነ ለማየት ወደ ሰዶምና ገሞራ እያቀና እንደነበረ ተናግሯል። እግዚአብሔር በከተማዪቱ ላይ የተነሣው «ጩኸት» ታላቅ እንደነበረ ተናግሯል። የጩኸቱ ድምፅ ከማን እንደ ተሰማ እንጃ። በከተማዪቱ ውስጥ ጻድቅ ሰው አልነበረም ማለት ይቻላል። ዳሩ ግን የአቤል ደም ለፍትሕ እንደ ጮኸ ሁሉ፥ እንዲሁም የፍርድ አስፈላጊነት ወደ እግዚአብሔር እንደሚጮህ ሆኖ

ቀርቧል። ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው። ምንም እንኳ እግዚአብሔር የከተሞቹን ሁኔታ አስቀድሞ ቢያውቅም፥ በፍርዱ ሁሉ ትክክለኛ እንደሆነ ሁላችንም እንድናውቅ፥ በከተማዪቱ ላይ የተመሠረተውን ክስ በጥንቃቄ መመርመር እንደነበረበት ተናግሯል። ምንም እንኳ ሰዎች ባመዛኙ በተሳሳተ መረጃ ላይ ተመሥርተው ቢፈርዱም፥ ሁሉንም ነገር የሚያውቀው እግዚአብሔር፥ ሁል ጊዜም በትክክልና ያለ አድልዎ ይፈርዳል።

ከዘፍጥረት 18፡22-32፥ አብርሃም ለሰዶም ከተማ ሲግልድ የሚያመለክት ገለጻ እናገኛለን። ምልጃ አንድ ሰው ለሌላው ሰው ወደ እግዚአብሔር የሚጸልይበት አንዱ የጸሎት ዓይነት ነው።

39ኛ ጥያቄ፤ ሀ) ሌሎች የጸሎት ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው?

ለ) ብዙውን ጊዜ የትኛውን የጸሎት ዓይነት ታዘወትራለህ?

ሐ) የምልጃ ጸሎት የሚያስፈልገው ለምንድነው?

አብርሃም በሦስት አበይት ነገሮች ላይ አትኩሮ ነበር። በመጀምሪያ፥ ብዙ ሰዎች በሰዶም ከተማ እንዲሞቱ አልፈለገም ይሆናል። የእግዚአብሔር ሰዎች፥ እግዚአብሔር በሚፈርድባቸው ጊዜም ቢሆን በሰዎች ላይ በሚወርደው የሞት ጽዋ አይደሰቱም። ስለ ፍጻሜ ዘመን ሲወሳ ከሁሉም የከፋው ነገር፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ያላመኑ ሰዎች፥ በነጩ የእግዚአብሔር ዙፋን ፊት መጣላቸው ነው (ራእይ. 20፡11-15)። ይህ እውነት ሰዎች ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ለማመን እንዲመርጡ ለመመስከር ሊያነሳሳንና ልባችንን ሊሰብረው ይገባል።

ሁለተኛ፥ አብርሃም ስለ ወንድሙ ልጅ ሎጥ አስቦ ነበር። ሎጥ በሰዶም ከሚገኙት ሰዎች ሁሉ ጋር እንዲጠፋ አብርሃም አልፈለገም ነበር።

ሦስተኛ፥ አብርሃም ስለ እግዚአብሔር ስም ቀንቶ ነበር። እግዚአብሔር በፍትሕ እንደሚፈርድ አብርሃም ያውቅ ነበር። ጻድቃንን ከኃጢአን ጋር ግጥሩት ለእግዚአብሔር ትክክለኛ ፍርድ እንደማይሆን አብርሃም ያውቅ ነበር። ፍትሕ ግለት የነዚያ ቅጣት የሚገባቸው ሰዎች ብቻ መቀጣትና የጻድቃን መሸለም ነው። አብርሃም «የምድር ሁሉ

ፈራጅ በቅን ፍርድ አይፈርድምን?» ብሏል። እግዚአብሔር ጻድቁንና ኃጢአተኛውን በአንድነት ቢያጠፋቸው ኖሮ፥ ሰዎች አድሎአዊ አምላክ እንደሆነ አድርገው ይወቅሱት ነበር። ቅን ፈራጅ አይሆንም ነበር። አብርሃም እግዚአብሔር ቅን ፈራጅ መሆኑን ስለሚያውቅ ነበር ለሰዶም ከተማ ለመማለድ የደፈረው።

አብርሃም ለእግዚአብሔር ባቀረበው ጸሎት፥ ባለማቋረጥ ጥያቄውን እያቀለለ ሄዶ ነበር። በመጀመሪያ፥ ሃምሳ ጻድቃን ቢኖሩ እግዚአብሔር ከተማዪቱን ያድናት እንደሆነ ይጠይቃል። ከዚያ አርባ-አምስት፥ አርባ፥ ሠላሳ፥ ሃያ፥ በመጨረሻም አሥር። በዚህ ሁሉ ጥያቄው፥ እግዚአብሔር ያንን ያህል ጻድቃን ቢኖሩ ከተማዪቱን እንደሚያድናት ተናግሯል። እግዚአብሔር የወዳጁን የአብርሃም ጸሎት አደመጠ። ለምን አብርሃም በአሥር ላይ እንዳቆመ አንዳንድ ሰዎች ይደነቃሉ። ምናልባት አብርሃም በአሥር ላይ ያቆመው ስለ ሎጥ ቤተሰቦች ያስብ ስለ ነበረ ይሆናል። አንዳንድ ሰዎች የሎጥ ቤተሰብ ሎጥንና ሚስቱን (2)፥ ሁለት ወንዶች ልጆች (2)፥ ያገቡ ሴቶች ልጆቹና ባሎቻቸው (4) እና ያላገቡ ሴቶች ልጆችን (2) ያጠቃልል እንደ ነበር ያስባሉ (ዘፍ. 19፡12-14)። ይህ በድምር አሥር ይሆናል። ይህ ቁጥር የተመሠረተው መላእክት ስለ ሎጥ ወንዶች ልጆች፥ ስለ ሴቶች ልጆቹና ስለ አማቾቹ ባቀረቡት ጥያቄ ላይ ነው (ዘፍ. 19፡12)። የሎጥ ልጆች ትክክለኛ ቁጥር ስለማይታወቅ፥ ሴቶች ልጆቹ አግብተው እንደሆነ ወይም በእርግኝነት ደረጃ እንደሚገኙ አከራካሪ ነው።

40ኛ ጥያቄ፤ - ከዚህ ታሪክ ውስጥ የምንማራቸው እነዳንድ ትምህርቶች ምንድናቸው?

ከዚህ ታሪክ ውስጥ የምንማራቸው በርካታ ጠቃሚ ነጥቦች አሉ። በመጀመርያ፥ ምናልባት ሙሴ እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን እንደሚቀጣ በመግለጽ እስራኤልንና እኛን ለማስጠንቀቅ ይፈልጋል። ምንም እንኳ የዓለም ሕዝቦች እየበለጸጉ ቢሄዱና ቅጣታቸውም የራቀ ቢመስል፥ አንድ ቀን እግዚአብሔር በሞት ይፈርድባቸዋል። አንዳንድ ጊዜ ይህ ሥጋዊ ሞት ነው። እንዲሁም የዘላለም ሞት መሆኑን እናውቃለን። ፈራጁ እግዚአብሔር እንደማይቀጣ አድርገን ራሳችንን

ማሳመን የለብንም። ኢየሱስ እንዳለው፥ ከጥፋት ውኃ በፊት የነበሩ ሰዎች እንደሚሞቱ ሳያውቁ፥ ይበሉና ይጠጡ ነበር (ማቴ. 24፡36-39)። ከኃጢአተኞች ጋር እንዳንጠፋ፥ በእግዚአብሔር ፊት የጽድቅን ሕይወት መኖር አለብን።

ሁለተኛ፥ እግዚአብሔር እውነተኛ ጽድቅ ያለበትን ሰው ልብ ለማሳየት ይፈልጋል። አብርሃም ከሰዶም ውድቀት ርቆ ነበር። የወንድሙ ልጅ ግን አብርሃምን በመተው፥ በሰዶም ርኩሰት ውስጥ ይኖር ነበር። አብርሃም ለሚሆነው ነገር ግዴለሽ ለመሆን ይችል ነበር። ዳሩ ግን አብርሃም ሩኅሩኅ ልብ ስለ ነበረው፥ ስለሚጠፉት ይጨነቅ ነበር። እኛም እንደዚሁ፥ ለጠፉትና ለዘላለም የሲዖል ኑሮ ለሚፈረድባቸው ሰዎች ሩኅሩኅ ልቦና ሊኖረን ይገባል። ይህ ወንጌሉን ለጠፉት ሰዎች ለማካፈል ሊያበረታታን ይገባል።

ሦስተኛ፥ እግዚአብሔር ስለ ባሕርይው ሊያስታውሰን ይፈልጋል። እርግጥ ነው እግዚአብሔር የፍቅር አምላክ ነው። ደግሞም እግዚአብሔር ቅን ፈራጅ አምላክ ነው። ፍትሕ ሁለት ገጽታዎች አሉት። በመጀመሪያ፥ የሽልማት ገጽታ አለው። እግዚአብሔር ሰዎችን በጥቅሉ አይቀጣም። ጻድቁን ይሸልማል። ደግሞም ፍትሕ የቅጣት ገጽታም አለው። እግዚአብሔር ኃጢአትን ሳይቀጣ አያልፍም። ኃጢአተኛው ይጠፋል።

41ኛ ጥያቄ፤ ሀ) እግዚአብሔር እያንዳንዱ ሰው እንዳሻው እንዲኖር ቢፈቅድና ጻድቁን ባይሸልም ወይም ኃጥኡን ባይቀጣ፥ የሚከፋው እምኑ ላይ ነው?

ለ) የእግዚአብሔርን ፍትሕ ከሰው ጋር አወዳድር።

አራተኛ፥ እግዚአብሔር አንድ አስፈላጊ እውነት ለማስተማር ይፈልጋል። እግዚአብሔር አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ጻድቃን በሰዶም ከተማ ውስጥ ቢኖሩ ከተማዪቱን ለማዳን ፈቃደኛ ነበር። ጻድቃን ልክ እንደ ጨውና ብርሃን ናቸው። ሕብረተሰብ ወይም ሕዝብ ሙሉ ለሙሉ እንዳይደመሰስ ለመጠበቅ ይረዳሉ። ጻድቃን ሳይኖሩ ሲቀሩ ወይም ጻድቃን ዓለምን ሲመስሉ፥ ክፉን ለመቋቋም የሚችል ነገር ስለማይኖር፥ የእግዚአብሔር ቅጣት ይከተላል። ምንም እንኳ በማንኛውም አገር

ውስጥ የክርስቲያኖች ቁጥር ባብዛኛው አናሳ ቢሆንም፥ የሚያስገርመው እውነት ሕዝቡ በምግባር ብልሹነት ውስጥ እንዳይዘፈቅ ጠቃሚ ሚና መጫወታቸው ነው። ሕዝቡን ከጥፋት ለማትረፍ ይረዳሉ።

ዳሩ ግን፥ ይህ አስቸጋሪ ጥያቄዎችን ያስነሣል። ጻድቁም ከኃጥኡ ጋር የሚሰቃይባቸው ጊዜያት አሉ- በረሃብ፥ በመሬት መንቀጥቀጥ፥ ወዘተ። ጻድቃን ሰዎችም እንደ ኃጥአኑ ይሞታሉ። ለምን? መልሱን ሁል ጊዜም አናውቅም። ዳሩ ግን ክርስቲያኑ ሊያስታውስ የሚገባው አስፈላጊ ነገር ከኢየሱስ ትንሣኤ ወዲህ፥ ሞት አንዳች መውጊያ እንደሌለው ነው (1ኛ ቆሮ. 15፡5-56)። ለእግዚአብሔር ልጆች፥ ሞት እግዚአብሔር ወዳለበት ወደ መንግሥተ-ሰማይ እንዲገቡ ምክንያት የሚሆን ነገር ነው። ለእግዚአብሔር ፍርድ ስለሚያዘጋጀው፥ ሞት መውጊያ የሚኖረው በኃጢአተኞች ላይ ነው። ምንም እንኳ ጻድቅ በምድር ላይ ቢሰቃይም፥ ይህ ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው። ጻድቃን ከእግዚአብሔር ጋር በመንግሥተ-ሰማይ ስለሚሆኑ፥ ከፈታቸው ዘላለማዊ ደስታ ይጠብቃቸዋል።

42ኛ ጥያቄ፤ - ይህ ለክርስቲያኖች በመከራ ጊዜያት ትልቅ መጽናናት የሚሆነው እንዴት ነው?

አራተኛ ቀን ፡- ዘፍጥረት 19

በዓለም ውስጥ ሦስት ዓይነት ሰዎች አሉ። በመጀመሪያ፥ ለደኅንነታቸው በግላቸው በኢየሱስ ክርስቶስ ያላመኑ ሰዎች አሉ። ከአራት ቢሊዮን ከሚበልጡ የዓለም ሕዝቦች መካከል፥ እጅግ የሚበዛው ክፍል በዚህ ምድብ ውስጥ ይገኛል።

ሁለተኛ፥ ፈሪሃ-እግዚአብሔር ያላቸው ክርስቲያኖች አሉ። እነዚህ ሕይወታቸውን ሙሉ በሙሉ እግዚአብሔርን ለመከተል የሰጡ ክርስቲያኖች ናቸው። እንደ አብርሃም ያሉ ናቸው። ምንም እንኳ ኃጢአት ሊያደናቅፋቸው ቢችልም፥ ንስሐ ገብተው እግዚአብሔርን ወደ መታዘዝ ሕይወት ይመለሳሉ። የሚያሳዝነው፥ በዚህ ክፍል ሊመደቡ የሚችሉ ጥቂት ቁጥር ያላቸው ክርስቲያኖች መሆናቸው ነው።

ሦስተኛ፥ ዓለማዊ የሆኑ ክርስቲያኖችም አሉ። እነዚህ ሰዎች ክርስቲያኖች እንደሆኑ ቢናገሩም፥ በሚኖሩት ኑሮ ለእግዚአብሔር ክብር አይኖሩም። በዓለም ተጽዕኖ ሥር የወደቁና የዓለምን ነገሮች የሚወዱ ናቸው። አስተሳሰባቸው ከዓለም ጋር ይመሳሰላል። ሎጥ ለዓለማዊ ክርስቲያን ጥሩ ምሳሌ ነው።

43ኛ ጥያቄ፤ ሀ) ወደ ቤተ ክርስቲያንህ ስለሚሄዱት ክርስቲያኖች አስብ። ብዙዎች የሚገኙት ፈሪሃ-እግዚአብሔር ባላቸው ክፍል ውስጥ ነው ወይስ በዓለማውያኑ? አብራራ።

ለ) ልዩነቱን እንዴት ታሳያለህ?

ሐ) ለዓለማዊያን ክርስቲያኖች ምን መልእክት ልንነግራቸው ይገባል?

44ኛ ጥያቄ፡- ዘፍ. 19ን አንብብ።

ሀ) ወደ ሰዶም የሄዱት ስንት ሰዎች ነበሩ?

ለ) ሎጥ የት ነበር?

ሐ) ሎጥ ለሰዎቹ ምን አደረገላቸው?

መ) የሰዶም ሰዎች ኃጢአተኝነት የታየው እንዴት ነበር?

ሠ) ሎጥ ሰዎቹን ለማዳን ምን ለማድረግ ሞከረ? ይህ ስለ ሎጥ ምግባር ምን ያሳያል?

ረ) ሰዎቹ ሎጥን እንዴት አዳኑት?

ሰ) ሎጥ አማቾቹ ሰዶምን ለቀው እንዲወጡ ለማሳመን በሞከረ ጊዜ ምን ሆነ?

ሸ) ሰዶምን ለቀው የወጡት ስንት ሰዎች ነበሩ?

ቀ) እነ ሎጥ ወደ ኋላ እንዳይመለከቱ ያዘዙት ለምንድነው?

በ) በሎጥ ሚስት ላይ የደረሰው ነገር ምን ነበር? ለምን?

ተ) ሎጥና ቤተሰቡ ካመለጡ በኋላ እንዴት ሆኑ?

ኀ) ከሎጥ የተገኙ ሁለት ነገዶች እነማን ናቸው?

45ኛ ጥያቄ፤ ሀ) በዘፍጥረት 11፡31 ላይ እንደተጠቀሰው ሎጥ ዑርን ከለቀቀበት ጊዜ አንስቶ እስከ ዘፍጥረት 19 ድረስ፥ የነበረውን መንፈሳዊ ሕይወት አሳይ።

ለ) ሎጥ እንዴት ሊወድቅ ቻለ?

ሐ) ከዚህ ውስጥ ለመንፈሳዊ ጉዞአችን ምን ትምህርት እንማራለን?

1. የሰዶም መደምሰስ (19፡1-29)

ትናንትና ሦስት ሰዎች፥ ማለትም ሁለት መላእክትና እግዚአብሔር እንዴት አብርሃምን በከነዓን እንደጎበኙት ተመልክተናል። ከዚያም እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር እየተነጋገረ ሳለ፥ ሁለቱ መላእክት ጉዞአቸውን ወደ ሰዶም አቀኑ። እርግጠኛነቱን ባናውቅም፥ እግዚአብሔር ከአብርሃም በተለየ ጊዜ ወደ ገሞራ ሂዶ ይሆናል። ዳሩ ግን የዘፍጥረት 19 ታሪክ የሚያተኩረው፥ በሰዶምና በሎጥ ቤተሰብ ላይ በተፈጸሙት ክስተቶች ላይ ነው።

ሁለቱ ሰዎች ወደ ሰዶም በደረሱ ጊዜ፥ ሎጥን በከተማዪቱ በር ላይ ተቀምጦ አገኙት። ስለ ሎጥ የምናገኘው የመጀመሪያው ምልክት በጣም ጥሩ ነው። በጥንት ልማዶች፥ የፍርድ መስጫ ችሎት የሚገኘው በከተማዪቱ በር ባለው ግቢ ውስጥ ነበር። የከተማዪቱ ሽማግሌዎች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ፍርድ የሚሰጡት በዚህ ሥፍራ ተቀምጠው ነበር። ምንም እንኳ ሎጥ የዚያ ከተማ ሰው ባይሆንም፥ በዚያ የተከበረና በሰዶም ከተማ ሽምግልና ውስጥ እንዲሳተፍ የተፈቀደለት ሰው ነበር። ማንነታቸውን ባያውቅም ልክ እንደ አብርሃም፥ ሁለቱን ሰዎች እንደ ተመለከታቸው፥ ወዲያው ወደ ቤቱ ጋበዛቸው። ምናልባት ተራ ሰዎች እንዳልነበሩ ተረድቶ ሊሆን ይችላል። ዳሩ ግን የከተማዪቱን ታላቅ ኃጢአት ስለሚያውቅ፥ በተለይ ወደ ቤቱ ውስጥ እንዲገቡ ለመናቸው። ምንም እንኳ በመጀመሪያ ይህን ለማድረግ ባይፈልጉም፥ ሎጥ በመጨረሻ እሺ አሰኛቸው። አለመፈለጋቸው ምናልባት ከሰዶም ከተማ መጥፎ ስም የተነሣ ሊሆን ይችላል። ሎጥ መልካም እንግዳ ተቀባይ በመሆኑ፥ የሚበሉትን ምግብ በፍጥነት አዘጋጀላቸው። ምግቡ እውነት

«ቂጣ» ለመሆኑ ማረጋገጫው በፍጥነት ለመዘጋጀት መቻሉ ነበር። አብርሃም እንዳዘጋጀው ዓይነት ድግስ አልነበረም።

ወዲያውኑ ችግሮች ተፈጠሩ። የሰዶም የከተማ ሰዎች በሙሉ ከልጅ እስከ አዋቂው፥ እንግዶች በሎጥ ቤት ውስጥ እንደነበሩ ሰሙ። መጥተውም ሎጥ እንግዶቹን እንዲሰጣቸውና የግብረ-ሰዶም ግንኙነት እንዲፈጽሙባቸው ጠየቁት።

ይህ ታሪክ በሰዶም ከተማ የነበረውን የምግባር ብልሹነት የሚያመለክቱ ሁለት መረጃዎቹን ያቀርባል። በመጀመሪያ፥ የእንግዶች መብት ወይም እነርሱን የመንከባከቡ ጉዳይ አይከበርም ነበር። እንደ ኢትዮጵያ የጥንት ባሕል ባላቸው አገሮች፥ ለእንግዶች መልካም አቀባበል ማድረግ የተለመደ ነበር። እንግዳ ተቀባዩ እንግዶቹን የመጠበቅ ግዴታ ነበረበት። ሁለተኛ፥ የሰዶም ሰዎች ከሴቶች ጋር እንኳ የወሲብ ግንኙነት ለማድረግ አይፈልጉም ነበር። ከሌሎች ወንዶች ጋር የወሲብ ግንኙነት ለማድረግ ነበር ፍላጎታቸው። ይህ «የተመሳሳይ ጾታዎች ግንኙነት» («ግብረ-ሰዶም») ይባላል።

46ኛ ጥያቄ፤ - ሮሜ 1፡24-27 አንብብ።

ሀ) የተመሳሳይ ጾታዎች ግንኙነት ከተቃራኒ ጾታዎች ግንኙነት የከፋ የምግባር ዝቅጠት እንዳለው ሆኖ የተገለጸው እንዴት ነው?

ለ) የተመሳሳይ ጾታዎች ግንኙነት ኃጢአት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታይ ችግር ነውን? መልስህን አብራራ።

የሰዶም ከተማ ዛሬ በአንዳንድ የዓለም አገሮች ከሚገኙ ሰዎች ጋር ተመሳሳይ ነበረች። ወንዶች ለሴቶችና ሴቶች ለወንዶች ሊኖራቸው ከሚገባው ተገቢ የወሲብ ግንኙነት ፈንታ፥ የግብረ-ሰዶም ፈጻሚዎች ወንዶች ከወንዶችና ሴቶች ከሴቶች ጋር የሚፈጽሙት ግንኙነት ትክክል ይመስላቸዋል። ይህ በሮሜ 1 ከሰው ምግባረ-ብልሹነት አንዱ አካል እንደሆነ ተገልጾአል። እግዚአብሔር ጀርባቸውን ለእርሱ በሚሰጡት ሰዎች ላይ ፍርዱን ያመጣል።

አሁን የሎጥ ምስል በመለወጥ ላይ እንደነበረ ሊታየን ይጀምራል። ሎጥ እንዴት በሰዶም ክፋት እንደተለወጠ ልንመለከት እንችላለን። ሕዝቡን እንዲሁ በመቃወም ፈንታ፥ የወሲብ ግንኙነት እንዲያደርጉባቸው ልጃገረድ የሆኑ ልጆቹን ያቀርብላቸዋል። ለሴት ልጆቹ ምንም ግድ አልነበረውም።

የሰዶም ሰዎች ይህን ስጦታ አልተቀበሉም። ወዲያውኑ ቁጣቸው በሎጥ ላይ ገነፈለ። አስቀድመው ቢያከብሩትና ከሽማግሌዎቻቸውም ውስጥ አንዱ ቢያደርጉትም፥ አሁን ግን «እንግዳ» ተባለ። ምንም እንኳ ሎጥ ሁለቱን ሰዎች ለማዳን ቢሞክርም፥ በምትኩ ግን ሁለቱ ሰዎች ሎጥን አዳኑት፤ ሎጥን ስበው ወደ ቤት ካስገቡት በኋላ፥ ሰዎቹን በጊዜያዊ ዓይነ-ስውርነት መቷቸው።

የሰዶም ከተማ የምትፈተንበት ጊዜ አብቅቶ ነበር (ዘፍ. 18፡20-21)። የከተማዪቱም ኃጢአት ተረጋገጠ። ስለሆነም አሁን ለእግዚአብሔር ኃጢአተኞቹን የሚያጠፋበት ጊዜ ነበር። ሆኖም ለአብርሃም ሲል (ዘፍ. 17፡29)፥ እግዚአብሔር ሎጥን ለማትረፍ ወሰነ።

ሎጥ ከተማዪቱ ከመጥፋቷ በፊት ቤተሰቡን ለሽሽት እንዲያዘጋጅ መላእክቱ አስቸኮሉት። የሎጥ ቤተሰብ አባላት ስንት እንደሆኑ በግልጽ አልተጠቀሰም። መላእክቱ ስለ አማቾቹ፥ ስለ ወንዶችና ሴቶች ልጆቹ ጠይቀውታል። ይህ ማለት እነዚህ የተጠየቁት ሁሉ ነበሩ ማለት ነው። ዘፍ. 19፡14 በሁለት መንገዶች ሊተረጎም ይችላል። ይኸውም፥ አንድም ሴት ልጆቹን ያገቡ አማቾች ነበሩት ማለት ሊሆን ይችላል። እንዲህም ከሆነ፥ ሎጥ ያላገቡ ሁለት ልጃገረዶች ልጆች ነበሩት ማለት ነው (ቁ. 8)። ወይም ልጃገረዶቹ ለሁለት ሰዎች ታጭተው ነበር ማለት ይሆናል። እነኝህም የሎጥ የወደፊት አማቾች መሆናቸው ነው።

ሎጥ ለአማቾቹ ስለሚመጣው ፍርድ ሲነግራቸው፥ የሚያፌዝባቸው መሰላቸው። ሎጥ ግብዝ ሰው ነበር። በሰዶም ከተማ ውስጥ ለረዥም ጊዜያት እንደመኖሩ፥ ሕይወቱም ከሰዶማውያን ሕይወት ጋር የሚመሳሰል ነበር። ስለሆነም በሕዝቡ መካከል መልካም ክርስቲያናዊ ምስክርነት አልነበረውም። ልክ እንደራሳቸው አድርገው ይመለከቱት

ነበር። በሰዶም ላይ ስለሚመጣው እውነት በነቃና አማኞቹን ለማዳን በሞከረ ጊዜ፥ ግብዝነቱ በሁሉም ዘንድ የታወቀ ነበረና ከዚህ የተነሣ፥ አማኞቹ ሳያምኑት ቀሩ።

47ኛ ጥያቄ፥ - ሀ) ሎጥ ግብዝነቱን ያሳየው እንዴት ነበር?

ለ) በቤተ ክርስቲያንህ ብዙ ክርስቲያኖች ግብዝነታቸውን እንዴት ያሳያሉ?

የፍርዱ ጊዜ ደረሰ። መላእክቱ ሎጥንና ሚስቱን፥ እንዲሁም በቤቱ ውስጥ የነበሩትን ሁለት ልጃገረዶች፥ ከተማዪቱን እንዲለቁ አስቸኮሉዋቸው። ለሎጥና ለቤተሰቡ ከተማዪቱን ለቅቆ መውጣት ምን ያህል አስቸጋሪ እንደ ነበር አስብ። በራሳቸው ፈቃድ ለመልቀቅ አልፈለጉም ነበር። መላእክቱ በጉልበት ከከተማዪቱ ውስጥ ጎትተው ማስወጣት ነበረባቸው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው «እግዚአብሔር ለእነርሱ ምህረትን አብዝቶላቸው ነበር»። ከተማዪቱን በመልቀቅ ላይ ሳሉ፥ አንደኛው መልአክ ሩጠው ነፍሳቸውን እንዲያድኑ እንጂ፥ ወደ ኋላ እንዳይመለከቱ አዘዛቸው።

ዳሩ ግን ሎጥ ከሚስቱ ጋር በማምለጡ አልረካም ነበር። የግል ንብረቱ ሁሉ በሰዶም ከተማ ቀርቷል። ዳሩ ግን ወደ አብርሃም ከመመለስ ወይም በበረሃ ውስጥ ከመኖር ይልቅ፥ ዞዓር ወደ ተባለች ከተማ ለመሄድ እንዲፈቅድለት መልአኩን ለመነው። አብርሃም ለሰዶም ከተማ በመማለድ መንፈሳዊ ብስለቱን ሲያሳይ፥ ሎጥ ግን ለግል ሕይወቱ ብቻ በማሰብ ራስ-ወዳድነቱን አሳይቷል። መላእክቱ በመጨረሻ የሎጥን ጥያቄ ተቀበሉ።

ሎጥ ወደ ዞዓር በደረሰ ጊዜ፥ ጥፋቱ ተጀመረ። መጽሐፍ ቅዱስ «እግዚአብሔር በሰዶምና በገሞራ ላይ ከሰማይ እሳትና ዲና አዘነበ» ይላል። ከተሞቹ ብቻ ሳይሆኑ፥ ሚዳማው ሥፍራና ሌሎችም ከተሞች ወደሙ። ከብዙ ዓመታት በፊት ሎጥ የሚዳውንና የከተሞቹን ውበት የተመለከተ ሲሆን፥ አሁን ግን እግዚአብሔር በሰው ዓይን ፊት ማራኪና በእግዚአብሔር ዓይን ፊት ግን አስቀያሚ የነበረውን ያንን ሥፍራ አጥፍቶታል። ዛሬ እነዚህ ከተሞች የነበሩበት የሙት ባሕር አካባቢ ምድረ በዳ ነው። ብዙ ምሁራን ከተሞቹን ያጠፋ ድንገተኛ

የእሳተ-ገሞራ ፍንዳታ ሳይሆን እንደማይቀር ያስባሉ። እዚህ ላይ ማስታወስ የሚያሻው ትልቁ ነገር፥ ይህ ተፈጥሮአዊ የሚመስለው ቀውስ ከእግዚአብሔር ዘንድ መምጣቱን ነው። እግዚአብሔር በኃጢአታቸው ፈረደባቸው።

ሎጥ የሰዶምን ከተማ ለመልቀቅ ያልፈለጉትን አንዳንድ ቤተሰቦች አጥቷል። አሁን ደግሞ ሚስቱን አጣ። የመልአኩን ትዕዛዝ በመጣስ፥ የሎጥ ሚስት ወደ ኋላ ዞራ የሰዶምን ከተማ አየች። ይህ ተራ ዕይታ አልነበረም። የሰዶምን ከተማ የተመለከተችው በፍቅርና በናፍቆት ዓይን ነበረ። በከተማዪቱ ውስጥ የሚፈጸሙ የክፋት ልምምዶች ሁሉ ተዋህደዋት ስለ ነበር፥ ሰዶምን ትወዳት ነበር። እግዚአብሔር ወዲያውኑ በዚህች ሴት ላይ በመፍረድ፥ ወደ ጨው አምድነት ለወጣት።

48ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) እግዚአብሔር እንዲህ ከባድ ፍርድ የበየነባት ለምን ይመስልሃል?

ለ) ከዚህስ ስለ እግዚአብሔርና ስለ ኃጢአት ምን እንማራለን?

2. ሎጥ ከሁለት ሴት ልጆቹ ልጆች ወለደ (19፡30-38)

ይህ በዘፍጥረት ታሪክ ውስጥ ስለ ሎጥ የምናገኘው የመጨረሻ ክፍል ነው። የእግዚአብሔርን በረከቶች ከአብርሃም ጋር በደስታ ተከፍሎ ለነበረ ሰው፥ ይህ እንዴት የሚያሳዝን ፍጻሜ ነው! እንደ ኖኅ ታሪክ ሁሉ፥ ሎጥ ምንም እንኳ ከጥፋት ቢያመልጥም፥ ወዲያውኑ ለውርደት ተዳረገ። እግዚአብሔር የሰዶምና ገሞራን ክፉ ከተሞች ቢያጠፋም፥ በሎጥና በሴት ልጆቹ ውስጥ የነበረውን ክፋት አላጠፋም ነበር። ከዚህም የተነሣ ታላቅ ኃጢአት ተፈጸመ።

ሎጥና ልጆቹ የዞዓርን ከተማ የለቀቁበትን ምክንያት ባናውቅም፥ ምናልባት በጎብረተሰቡ ስለተገለሉ ይሆናል። ወደ አብርሃም መመለስ ሲገባቸው፥ ወደ ተራሮች በመሄድ በዋሻ ውስጥ መኖር ጀመሩ። በዚህ ጊዜ በጣም ድሆች እንደነበሩ አይጠረጠርም። የሎጥ ሁለቱ ሴት ልጆች ጋብቻ የመመሥረታቸው ተስፋ ተሟጦባቸዋል። ዳሩ ግን የቤተሰባቸው ሐረግ እንዲቀጥል ስለፈለጉ፥ አባታቸውን ለማጠጣትና በሰከረም ጊዜ በየተራ ከእርሱ ጋር ለመተኛት ተስማሙ። ከዚህም የተነሣ፥ ሁለት ወንዶች ልጆች ተወለዱ። ቀደም ሲል ሎጥ ልጆቹን ሰዶማውያን

የወሲብ ግንኙነት እንዲፈጽሙባቸው ቢሰጣቸውም፥ አሁን ግን እነርሱ ለወሲብ ተጠቀሙበት። ሁለቱ ልጆች ሞዓብ እና አሞን ተብለው ተጠሩ። ሞዓብ የሚለው «ከአባታችን» ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል ጋር ይመሳሰላል። ሁለተኛው ልጅ አሞን ማለት «የወገኔ ልጅ» ወይም «ዘመዴ» ማለት ነው። ሁለቱም ሰሞች የሎጥ ሴት ልጆች ከአባታቸው ጋር ያደረጉትን አሳፋሪ ግንኙነት ያንጸባርቃሉ።

አሁንም የዘፍጥረት ጸሐፊ፥ የአንዳንድ ነገዶች ጅማሬዎች፥ የትውልዶቻቸውን የምግባር ባሕርይ እንደሚያሳዩ ያመለክታል። ሞዓባውያንና አሞናውያን (የአሞን ትውልዶች) ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ-ምሥራቅ፥ በእስራኤል ዳርቻዎች ኖረዋል። በኋላም የሕዝበ-እስራኤል ፈታኝ ጠላቶች ሆነዋል (3፡12-30፤ 2ኛ ሳሙ. 8፡2፤ 10፡1-19)።

49ኛ ጥያቄ፤ - በማየት ሳይሆን፥ እንዴት በእምነት መመላለስ እንደሚቻል፥ ከሎጥ ሕይወት አንዳንድ ትምህርቶችን ዘርዝር።

ሎጥ የዓለማዊ ክርስቲያን ምሳሌ ነው። ውድቀቱን ከተመለከትን፥ አንዳንድ አስፈላጊ ትምህርቶች ለመማር እንችላለን። ሎጥ ከአብርሃም ጋር አደገ። ምንም እንኳ ቃል ኪዳኑን ለመውረስ ባይችልም፥ ከአብርሃም ጋር ቢቀመጥ ኖሮ፥ ከእርሱ ጋር ይባረክ ነበር። ዳሩ ግን በድንኳን ከመቀመጥ ይልቅ፥ ለዓይኖቹ መልካም የመሰለውን ነገር መረጠ። ምርጫው በራስ-ወዳድነት ፍላጎቶች ላይ የተመሠረተ ነበር። በመጀመሪያ ወደ ሰዶም አቅራቢያ ሄደ፤ ከዚያም በሰዶም ከተማ መኖር ጀመረ። ወዲያውም ሰዶምና ከፉ ምኞቶችዋ ወደ እርሱ አመሩ። ከዚህም የተነሣ፥ ቁሳዊ ሀብቶቹን በሙሉ፥ ከቤተሰቡም የሚበዛውን በግጣትና ከገዛ ሴት ልጆቹ ሁለት ልጆችን በመውለድ የሕይወቱን ታሪክ አጠቃሏል። ምንኛ የምያሳዝን ፍጻሜ ነው! ከእግዚአብሔር ነገሮች በላይ ዓለምን መውደድ የሚያስከፍለው ዋጋ ምን ያህል የመረረ ነው!

ክርስቲያን፥ ዓለማዊ ክርስቲያን ለመሆን፥ ወደ ውድቀት ወዲያውኑ አያመራም። ወደዚያ የሚያመራው በሂደት ነው። ክርስቲያኑ እንደ ዓለም ለመኖር እስኪጀምር ድረስ፥ ቀስ በቀስ በዓለማዊ የአኗኗር ዘይቤ

እየተማረከ ይሄዳል። በዚህም አኗኗሩ ፋይዳ ያለው ነገር የሚያገኝ ይመስለዋል። እንዲያውም ከዓለም ሕዝብ ጋር ወዳጅነት ይመሠርታል። በመጨረሻው ግን፥ በዓለም ዘይቤ ይረታና ምስክርነቱ ይጠፋል። እግዚአብሔርም በፍርድ ይገናኘዋል።

ሙሴ ይህንን ታሪክ የጻፈው አንዳንድ እውነቶች ለማስተማር ነው። በመጀመሪያ፥ እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ያለውን ጥላቻ ለማሳየት ይፈልጋል። ሙሴ የሰዶምና ገሞራን ከተሞች ጥፋት እንደምሳሌ አድርጎ በመጠቀም፥ እግዚአብሔር በኋላ ላይ ለምን ከነዓናውያን ሙሉ በሙሉ እንዲጠፉ እንዳዘዘ ለማሳየት ይፈልጋል።

ሁለተኛ፥ እግዚአብሔር ከዓለም ጋር መመሳሰል ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ፥ ሕዝቡ ለሆኑት ለእስራኤላውያንና ዛሬም ለእኛ በማሳየት ሊያስጠነቅቅ ይፈልጋል። እጅግ የሚከፉትን አገሮችና ሕዝቦች እግዚአብሔር እንደሚያጠፋቸው ቃል ይገባል። የከነዓናውያንን የአኗኗር ዘይቤ ተከትለው ቢሆን ኖሮ፥ እግዚአብሔር እስራኤላውያንንም ባጠፋቸው ነበር።

ሦስተኛ፥ እግዚአብሔር ዓለምን መውደድ የሚያስከትለውን የመጨረሻ ውጤት ለማሳየት ይፈልጋል። ዓለምን እንዳንወድ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያዛል (1ኛ ዮሐ. 2፡14-17 ተመልከት)። ዓለም አንድ ቀን ትጠፋለች (ሉቃ. 17፡32)። ሎጥ ለዓለም ካለው ፍቅር የተነሣ፥ ሁሉንም ነገር አጣ። ፍቅራችንን ሁሉ ለዓለም ብንሰጥ፥ እኛም ሁሉንም ነገር እናጣለን። የሎጥ ሚስት፥ በደኅንነታቸው ምክንያት የተገላገሉትን ዓለማዊ መሻት፥ ወደ ኋላ ዞረው ዳግመኛ ለማግኘት የሚጓዙ ሰዎች ምሳሌ ነች።

50ኛ ጥያቄ፤ - በአንዳንድ ክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ እንዴት ተመሳሳይ ሁኔታዎች እንዳጋጠሙህ ግለጽ።

51ኛ ጥያቄ፤ - ዓለማዊ ክርስቲያን መሆን ስለሚያስከትለው አደጋ፥ የቤተ ክርስቲያንህ ሰዎች ለማስጠንቀቅ የምትጠቀምባቸውን መመሪያዎች ዘርዝር።

አምስተኛ ቀን፡- ትምህርቱን ከልስና ለሳምንታዊ ስብሰባ ለመዘጋጀት፥ የውይይት ጥያቄዎችን ተመልከት።

ሳምንታዊ ስብሰባ

1. ሳምንታዊ የአምልኮ ጊዜ

2. የጸሎት ጊዜ

3. የትምህርቱ ክለሳ

4. የውይይት ጊዜ

ሀ. 1) አብርሃምና ሣራ በራሳቸው ባሕላዊ ዘዴ ልጅ ለማግኘት ያደረጉት ሙከራ፥ በእምነት ስለመመላለስ ምን ያስተምረናል?

2) እነርሱስ ለምን እንደዚያ አደረጉ?

3) የዚህ ሙከራቸው፥ የአጭርና የረዥም ጊዜ ውጤቶች ምን ምን ነበሩ?

4) ዛሬ ክርስቲያኖች በእምነት ሳይሆን፥ በማየት ወደ መመላለሱ የሚያዘነብሉባቸውን ሁኔታዎች ግለጽ።

ለ. 1) በዘፍጥረት ውስጥ የተመለከትናቸውን የተለያዩ የእግዚአብሔር ስሞች ዘርዝር።

2) የእያንዳንዱ ስም ትርጉም ምንድነው?

3) ስለባሕሪዩና ከእርሱም ጋር ግንኙነት ስለምናደርግበት ሁኔታ፥ ከእግዚአብሔር ስሞች ውስጥ የምንማራቸው ነገሮች ምንድናቸው?

ሐ. 1) በእግዚአብሔር ፊት መመላለስ፥ ፍጹም መሆን፥ ፍትሕና ጽድቅ፥ ምን ማለት እንደሆነ ግለጽ።

2) ይህስ በአንድ ኢትዮጵያዊ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ነጋዴም ቢሆን፥ የመንግሥት ሠራተኛ፥ አስተማሪ፥ የቤት እመቤት ብትሆን የሚታየው እንዴት ነው?

መ. 1) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የግርዘት ዓላማ ምንድነው?

2) በኢትዮጵያ፥ ለኦርቶዶክስ ክርስቲያኖችና ለሌሎችም የግርዘት ዓላማ ምንድነው?

3) ሴቶች የሚገረዙት ለምንድነው?

4) ስለ ሴቶችና ወንዶች ግርዘት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማስተማር የሚገባን ምንድነው?

5) ግርዘት ከጥምቀትና ከቅዱስ ቁርባን ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

6) በዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የጥምቀትና የቅዱስ ቁርባን ዓላማ ምንድነው?

ሠ. 1) የሎጥን ውድቀት ዛሬ ከሚታየው የብዙ ክርስቲያኖች ውድቀት ጋር አወዳድር። የሚመሰሰሉት ወይም የሚለያዩት እንዴት ነው?

2) ሎጥ እንዳደረገው፥ ክርስቲያኖች በኃጢአት እንዳይወድቁ ለማስጠንቀቅ፥ በአብያተ ክርስቲያናችን ማስተማር የሚገባን ነገር ምንድነው?

5. ጸሎት።

ትምህርት ስምንት

ዘፍጥረት 20-23

የመጀመሪያ ቀን፡- ዘፍጥረት 20

አብርሃም ለብዙ ዓመታት ከእግዚአብሔር ጋር ተመላልሷል። በእነዚህም ዓመታት ውስጥ እምነቱ አድጓል። ባለፈው ሳምንት እግዚአብሔር ሰዶምን ለማጥፋት በነበረው እቅድ፥ ለአብርሃም ምሥጢሩን በማሳወቅ እንዴት እንዳከበረው ተመልክተናል። እንዲሁም እግዚአብሔር፥ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ልጅ እንደሚወለድ የተስፋ ቃል ገብቶለታል። ምንም እንኳ አብርሃም በብዙ የሕይወት ክፍሎቹ በሳል ቢሆንም፥ ለግል ደኅንነቱ ግን በእግዚአብሔር የመተማመን ችግር አልፎ አልፎ ይታይበት ነበር። ዛሬም አብርሃም